አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሃግብር

# በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስው ትምህርትን ለመማር የሚጠቀሙባቸው የመማር ብልሃቶች ትንተና

(በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

ለአማርኛ ማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

በበቀለ አሹሮ አሎቶ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ፣ 2015 ዓ.ም.

# በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስው ትምህርትን ለመማር የሚጠቀሙባቸው የመማር ብልሃቶች ትንተና

(በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሃግብር

ለአማርኛ ማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

የጥናቱ አማካሪ

ዳዊት ፍሬሕይወት (ዶ/ር)

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረምረቃ መርሃግብር

በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስው ትምህርትን ለመማር የሚጠቀሙባቸው የመማር ብልሃቶች ትንተና (በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ ለተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር ማስትሬት ዲግሪ ማሟያ በበቀለ አሹሮ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

### የፈታኞች ቦርድ አባላት

አማካሪ_____________________________ ፊርማ___________________ ቀን_____________

የውጭ ፈታኝ________________________ ፊርማ _________________ ቀን_____________

የውስጥ ፈታኝ_________________________ ፊርማ___________________ ቀን_____________

# የአጥኚው ማረጋገጫ (Declaration)

ይህ “በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስው ትምህርትን ለመማር የሚጠቀሙባቸው የመማር ብልሃቶች ትንተና (በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር ማስትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የሆኑና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤት መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም_______________________________________

ፊርማ_________________________

ቀን________________________

# ምስጋና

ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ጀምሬ በሰላም እንዳጠናቅቅ ጤናዬን የሰጠኝ አልፋና ኦሜጋ የሆነው ቸሩ ልዑል እግዚአብሔር ስሙ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን፡፡

ውድ መምህሬና አማካሪዬ ዶ/ር ዳዊት ፍሬሕይወት ከርዕስ መረጣው ጀምረው ጥናታዊ ጽሑፉን በጥልቀት በማንበብ የተንጋደደውን በማቃናት፣ ገንቢ አስተያየትና ጥቆማ በመስጠት፣ በተለይም የመረጃ መተንተኛ መንገዶችን ደጋግሞ በማመላከትና በመፈተሽ ላደረጉልኝ ሙያዊ እገዛ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ የእውቀት፣ የክህሎትና የጥሩአመለካከት አባቴ በመሆናቸው ቸሩ ልዑል እግዚአብሔር ጤናና እድሜ በመስጠት ውለታቸውን ይክፈልልኝ፡፡ እንዲሁም መ/ር ተስፋዬ ሄልሶ፣ ር/መ/ር ታዬ በቀለ እና መ/ር ኢያሱ ዮሐንስ ስለማማከር ጥበባቸውና ችሎታቸው ልዩ አድናቆት አለኝ፡፡ በተጨማሪ ውድ ባለቤቴ አልጋነሽ አበበ ጥናትና ምርምር በማደርግባቸው ጊዜያት ከጎኔ ሳትለይ ላደረገችልኝን ሁሉ ምሥጋናዬ የላቃ ነው፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሚሆን ገንዘብ ወጪ በማድረግ ድጋፍና ትብብር ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# የይዘት ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና........................................ i

አህጽሮተ ጥናት........................................vi

ምዕራፍ አንድ........................................ 1

መግቢያ........................................ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 4

1.3 ዋና ዓላማ........................................ 6

1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት........................................ 6

1.5 የጥናቱ ወሰን ........................................ 7

1.6 የጥናቱ ውስንነት ........................................ 7

ምዕራፍ ሁለት ........................................ 9

ክለሳ ድርሳናት........................................ 9

2.1. የሰዋስው ትምህርት ምንነት ........................................ 9

2.2 የቋንቋን ሰዋስው የመማር ብልሃቶች........................................ 11

2.3 የቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሃቶች ክፍፍል/ምደባ........................................ 13

2.3.1 አእምሯዊ ብልሃቶች(cognitive strategies) ........................................ 13

2.3.2 ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች........................................ 13

2.3.3 ማህበራዊ ብልሃቶች(social strategies)........................................ 14

2.3.4 አካካሽ ብልሃቶች........................................ 15

2.3.5 ትውስታ ብልሐቶች ........................................ 15

2.3.6 ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች........................................ 15

2.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 15

ምዕራፍ ሶስት ........ 19

የጥናቱ ዘዴ ........ 19

3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 19

3.2 የናሙና አመራረጥ ........ 19

3.2.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ ........ 19

3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........ 20

3.2.3. የተማሪዎች አመራረጥ ........ 20

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 20

3.3.1 የጽሑፍ መጠይቅ ........ 20

3.3.2. ቃለ መጠይቅ ........ 21

3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 21

ምዕራፍ አራት ........ 23

የመረጃ ትንተና እና ውጤት ........ 23

4.1የርቱዕ መማር ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ........ 23

4.1.1 የአእምሮታዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ........ 23

4.1.2. ማህደር-ትውስታ ጥቅል መረጃ ትንተናና ውጤት ........ 32

4.1.3. የአካካሽ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ ትንተናና ውጤት ........ 38

4.2 ኢርቱዕ የመማር ብልሃቶች ........ 41

4.2.1 ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃትንተናና ውጤት ........ 41

4.2.2 የስሜት ነኪ ቁጥር ብልሃቶች ጥቅል መረጃ ትንተናና ውጤት ........ 45

4.2.3 የማህበራዊ ጥቅል መረጃ ትንተናና ውጤት ........ 49

ምዕራፍ አምስት ........ 54

ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች ........ 54

5.1.ማጠቃለያ ........ 54

ሀ) የርቱዕ የመማር ብልሃቶች ........ 54

ለ) የኢ-ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ........ 56

5.3 የመፍትሄ ሀሳብ ........ 58

አባሪ 1 ........ 65

ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ........ 65

አባሪ 2 ........ 74

ለተማሪዎች የቀረበቃለ መጠይቅ ........ 74

## የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1 የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ………………………. ............... ………30
ሠንጠረዥ 2 የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ…………………………............. ………33
ሠንጠረዥ 3 የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ…………………… ............... ……….36
ሠንጠረዥ 4 የማህደረ ትውስታ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ…………………............ …….39
ሠንጠረዥ 5 የአካካሽ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ…………………………….............. ……..44
ሠንጠረዥ 6 የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ………………… .............. ……48
ሠንጠረዥ 7 የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ጥቅል መረጃ………………… ........ ……....52
ሠንጠረዥ 8 የማህበራዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ………………………….... …………56
ሠንጠረዥ 9 የጽሑፍ መጠይቅ………………………………………………........... …….72

# አህጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የስዋሰው መማር ብልሃቶችን መተንተን ነው፡፡ ጥናቱ በዚህ አብይ ዓላማ ስር ከቋንቋ መማር ብልሃቶች መካከል የትኞቹን አዘውትረው በመጠቀም ትምህርቱን እንደሚከታተሉ መለየት ለሚሉት ንዑሳን ዓላማዎቹ ጥናቱ ምላሽ አስገኝቷል፡፡ ጥናቱ በደቡብ ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን አንጋጫ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ስድስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በተመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች ዘጠነኛ ክፍል የሚማሩ በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ 106 ከሦስቱም ትምህርት ቤት ተማሪዎች በቀላል እጣ ናሙና (Simple Random Sampling) ዘዴ በመውሰድ፣ በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ የተካሔደ ገላጭ ጥናት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የሁለተኛ ቋንቋ በቀላል ለመማር በተለያየ መንገድ እገዛ ያደርጋሉ በሚባሉት ርቱዕ እና ኢ-ርቱዕ ብልሃቶች ስር በቀረቡ ንዑሳን ብልሃቶች ላይ በማተኮር የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች  የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ሲማሩ ብልሃቶቹን ምን ያህል እንደሚጠቀሙባቸው ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት በሁለት የተደራጀ የጽሁፍ መጠይቅ አገግሎት ላይ ውሏል፡፡ እንደ አጋዥ መረጃ መሰብሰቢያነት ደግሞ ቃለ መጠይቅ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በተሰበበው መረጃ የትንተና ውጤት መሰረትም፣ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን የሚማሩበት መንገድ ለሰዋስው መማሪያ እገዛ የሚያደርጉትን የመማር ብልሃቶች በስፋት በመገልገል ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ በመረጃው መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በሰጡት መረጃዎች መሰራት በትንተናው ውጤት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አዳዲስ ሰዋስዋዊ ብልሃቶችን በመጠቀም በአዕምሯቸው በመስተወስ የቀደመውን እውቀታቸውን ከአሁኑ ትምህርት ጋር እያስተሳሰሩ መማር፣ይዘቶችን በማቧደን፣የሀረጋትን አወቃቀር መተንተንና ልዩ ልዩ ምልክቶችን መጠቀም የሚከብዱ መዋቅሮችን ከአፍ መፍቻ ቋንቋ በመፈለግ ማተካከት ለሰዋስው ትምህርታቸው ከመረጡአቸው ብልሃቶች ሰዋስውን ለመገንዘብ ዕቅድ ማውጠት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በፍጹም እንደመይጠቀሙ የተገኛው መረጃ ትንተና ውጤት ሲያመለክት እንደመፍትሄ የርቱዕና የኢ-ርቱዕ ብልሃቶችን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ይሁን በተግባቦት ሂደት ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን መንጋድ መምህረን ጥቆማ ቢሰጡ እና ተማሪዎች በራሰቸው ጥረት ኃላፊነት ወስደው ብልሃቶችን በሚገባ ቢያከነወኑ የተሸለ ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

አማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማ የተማሪዎችን የክሂል፣ የስነልሳንና የስነፅሁፍ እውቀቶችን ማበልፀግ ነው። ቋንቋ እንደበታዊና ስርአታዊ የሆነ የሰው ልጅ መግባቢያ መሳሪያ ነው። አማርኛ ከሴም የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል። በአገራችን የሥራ ቋንቋ በመሆን እያገለገሉ ይገኛል። በደቡብ ክልል ከሶስተኛ እስከ አሥረኛ ክፍል ድረስ እንደ አንድ ትምህርት ይሰጣል።

የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ በጣም ወሳኝ ነው። የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ከሚያግዟቸው በርካታ ነገሮች መካከል ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን በብቃት መጠቀም ነው። ይህን አስመልክቶ እንደተገለጸው የተማሪዎቹ ሰዋስውን የመማር ብልሃት እውቀትና ልምድ እየዳበረ ሲሄድ ከመምህሩ ቁጥጥር ወይም ጥገኝነት ተላቀው በክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በራሳቸው ጥረት ሰዋስውን ለመማር ያግዟቸዋል። ይህ ማለት ቋንቋን የማስተማሪያ ብልሃቶች ተማሪዎቹ ከመማሪያ ክፍል ውጭ ያለመምህራቸው እገዛ በራሳቸው ለመስራትና ራሳቸውን በራሳቸው ለመርዳት ያስችላቸዋል ማለት ነው(R. L. Oxford & Scarcella, (1994) እና Zhongganggao (2001)) ።

የድሮው ወይም የመጽሃፍ ዘዴ ሰዋስውን የማስተማሪያ ሂደት የተማሪውን ንቁ ተሳትፎ ከግምት ውስጥ ያላስገባና በትምህርቱ አቀራረብ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የሰዋስው እውቀታቸውንም ሆነ ክሂሎቶችን እንዲያዳብሩ ከማበረታታት ይልቅ መምህራን በሚያቀርቡላቸው ላይ እንዲወሰኑ እና በመምህራን ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው መሆኑ ነው(DeKeyser, 1995; R. L. Oxford & Scarcella, 1994):: ተማሪ መርና ተግባቦታዊ የትምህርት አቀራረብ ወይም ብልሃትን ትምህርት ተማሪው የሰዋስው ችሎታ መዳበር የድርሻውን ጥረት ማድረግ እንዳለበትና የራሱን ሚና መጫዎት እንዳለበት ነው። ይህም መሆን የሚችለው ተማሪው የመማር ማስተማር ሂደት 2 ዋና ተዋናይ ሆኖ በንቃት ሲሳተፉ ብቻ ነው። የተማሪው ንቁ ተሳትፎ ጠቀሜታው ለትምህርቱ ኃላፊነት የመቀበል ልምድ እንዲያጎለብት፤ ሥራውን በራሱ እየተቆጣጠረ የሰዋሰው ዕውቀቱን እንዲያሳድግ ነው(López-Jiménez, 2014)።

የሰዋስው ችሎታ የተለያዩ የሰዋስው መማሪያ ብልሃቶችን የመጠቀም ብቃትንም ያካትታሉ (O'Dell, Read, & McCarthy, 2000)፡፡ ከዚህ አኳያ የሰዋስው ትምህርት መስክ ሰዋስው ለማስተማርና ለመማር የሚያገለግል አያሌ የሰዋስው ትምህርት አቀራረቦች፣ ቴክኒኮችና ብልሃቶች ገልጸዋል (Alqahtani, 2015)፡፡ ከነዚህም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የሰዋስው ችሎታ ለማሻሻል የተማሪዎች የሰዋስው መማሪያ ብልሃቶች አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት ተሰቷል (Hulstijn, 2001; Lee, 2007)፡፡ ከዚህም የተነሳ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ወይም ሰዋስውን ማስተማር ተማሪዎች የራሳቸውን የሰዋስው እውቀት በራሳቸው መንገድ ለማስፋት የሚያስችሏቸው ተገቢ ብልሃቶች ማስገንዘብን ጭምር አላማው ያደረገ ነው (Nation, 2003; Pérez & Ruiz, 2007) ፡፡ ከዚህም ሌላ የሰዋስው እውቀት የተማሪዎችን ዓላማዎች ለማሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

በሰዋስው እውቀትና በአንብቦ መረዳት መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ (Chung & Nation, 2003; Hauptman, 2000) እንዳስረዱት የሰዋስው ሃይል በአንብቦ መረዳት፣በማንበብ መዝናናትና በመማር ስኬታማነት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል፣ ሰዋስው አንድን ጽሁፍ ሊያደናቅፍና ሊያቆም ይችላል፡፡ በተማሪዎች የሰዋሰው እውቀት እድገት ላይ በራስ የመማር ብልሃት አዎንታዊ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች አንዱና ዋናው መሆኑ ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡ ይህም ለሁለተኛ ቋንቋ በአግባቡ ለመጠቀም ወሳኝ መሆኑን ያመላክታል፡፡

እንደ ምሁራኑ ጥናት፣ ይህንን አስመልክተው ብልሃቶች የተማሪዎችን ሰዋሰው የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑንና አረፍተ ነገርና ሀረግ በትክክል በመስራት ችሎታ ጋር ጥብቅ ትስስር ያላቸው መሆኑን ተጠቁሟል፡፡ ይህም የሚገልጸው ያለ ሰዋሰው ችሎታ አንድን ቋንቋ ለመረዳት አዳጋች መሆኑን ነው (Rutherford, 2014; በላይነሽ, 2002)፡፡

ይህንን አስመልክቶ በዚህ ዙርያ ጥናት ያደረጉት አጥኚዎች እንዳስቀመጡት ከሆነ፣ የሰዋስው መማር ብልሃቶችን በግልጽ የተማሪዎች ንግንዛቤና አጠቃቀም ለማሳደግ ከተለመደው የሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴ በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ያሳዩበት ነበር፡፡ የተለያዩ ብልሃቶችን መጠቀምና መለማማድ ሰዋሰውን ለመማር ያለው ጠቀሜታ በጣም የጎላ ነው፡፡ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ በዋናነት ለሰዋስው ቅድሚያ በመስጠት መማርና ማሰላሰል እንደሚገባ የተለያዩ ጥናቶች ያስያሉ (Kemp, 2007; Rutherford, 2014)፡፡

ምሁራን እንደገለጹትም ሁለተኛ ቋንቋ መማር በዋናነት የቋንቋውን በሰዋስው የመማር ጉዳይ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ እንደምሁሩ አባባል ሀሳብን በሌላ ቋንቋ ሰዋስው እራስን ለመግለፅ በንግግር ሂደት የሚያሳድረው ፍርሃትና ጭንቀት ስሜትን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ የሚደግፍ የመማር ቀጥታ ትምህርት የማካለል ሂደት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ ለዚህም ትኩረት ያደረጉት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል ሲያልፉ በጽሁፍ ሆነ በንግግር ወቅት ከሚያጋጥማቸው ችግር አንድ የሰዋስው ዕውቀት በመሆኑ ብልሃቶችን ተጠቅመው መማር ያለውን እገዛ ለመተንተን በማሰብ ነው (Abdullaev, 2021; Hill & Hill, 1986)፡፡ ይህም ማለት አማርኛን በክፍል (ከትምህርት ቤት ውጭ) አይጠቀሙም ቤተሰብ ውስጥና በአካባቢው አፋቸውን የፈቱበትን ስለሚጠቀሙ ነው፡፡ ሰዋስውን የመማር ብልሃት ተማሪዎቹ ትኩረት አለመስጠትና ብልሃቶችን አለመጠቀም የሰዋስው ዕውቀት ማነስ ምክንያት ሊሆን ይችላል በማለት ይህን ጥናት ለማካሄድ ተነሳስቷል፡፡

የሰዋስው ዕውቀት ሀሳባቸውን አዳምጠውና አንብበው ለመረዳት ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እገዛ እንዳለው ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ (Tılfarlıoğlu & Yalçın, 2005)፡፡ Lukėnienė፣ ወይንሸት ታደሰ እንዳስቀመጡት፤ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን ከሌሎች ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ ማለትም በራሳቸው ለመማር ብልሃቱ ያግዛቸዋል (Lukėnienė, 2010; ወይንሸት ታደሰ, 2011) ደግሞ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግርና በጽሐፍ ለማስተላለፍም ሆነ የሌሎችን ሀሳብ አዳምጠው እና አንብበው ለመረዳት ይችሉ ዘንድ የሰዋስው ዕውቀት ሊኖራቸው እንደሚገባ ነው ያስረዱት፡፡ ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሀሳቦች እንደምንረዳው የሰዋስው ማስተማሪያ ብልሃቶች ተማሪው በራሱ መንገድና ጥረት አዳዲስ ሰዋስው የሚማርበትን ብልሃት እንዲያዳብር ለማበረታታት የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው የዘርፉ ምሁራን በአጽንኦት ይገልጻሉ (Bornay,2011)፡፡

ተመራማሪዎቹ ከላይ እንዳስቀመጡት ሰዋሰውን መማር በበርካታ መምህራንና ምሁራን ዘንድ ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት ተገቢ ያልሆነ እይታ መኖሩ፤ የሰዋሰው ትምህርት ሙሉ ትኩረት እንዳይሰጠው አድርጎ ቆይቷል በማለት ገልጸዋል፡፡ በዚህ ጥናት አፋቸውን በከምባትኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ የሰዋሰው ትምህርት መማሪያ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችን መተንተን ነው፡፡ የከምባትኛ ቋንቋ ከኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ሲሆን ከሶስተኛ እስከ አራተኛ ክፍል ድረስ እንደ አንድ ትምህርት መስጫ ቋንቋነት ሲያገለግል ከ5ኛ እስከ 10ኛ እንደ አንድ ትምህርት ይሰጣል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ በከምባታ ጠምባሮ ዞን ውስጥ

በሚገኝ በአንጋጫ ወረዳ አንጋጫ ሁለተኛ ደረጃትምህርት ቤት፣ በቀዕላማ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በፉናሙራ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት  አፋቸውን በከምባትኛ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መሆኑ የዚህ ጥናት አጥኝም አፋቸውን በከምባትኛ የፈቱ ተማሪዎች ለሰዋሰው ትምህርት የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ለመተንተን ተነሳስተዋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አቅራቢም አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ደረጃ (9ኛ እስከ10ኛ) ባስተማረባቸው ባለፉት 20 አመታት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን የሰዋስው ትምህርት ዓላማ በተገቢው መንገድ ተረድተው በደረጃቸው የሚቀርብላቸውን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተገቢው ሁኔታ ለይተው ለመጠቀም ችግር ሲገጥማቸው አስተውሏል፡፡

ሰዋስውን በክፍል ውስጥ ማስተማር እያገለገለ ያለው ሁኔታ፣ አቀራረቦችና ባህሪያቸውን ከገለጻዎቹ እንደተረዳነው ተማሪዎች የሚያስጨብጡት እውቀት አንደኛው በትርጉም ላይ ሌላው ደግሞ በቅርጽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ተማሪዎች የተሟላ እውቀት እንዲያገኙ የትኛውን ስልት መጠቀም የተሻለ እንደሆነ በማሳየት ብዙ ጥናቶች የተካሄዱ ሲሆን የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ የሆነው የሰዋሰው ትምህርት ከሚዳብርባቸው ቦታዎች መካከል ቀዳሚውን ቦታ የሚይዙት ትምህርት ቤቶች በመሆኑ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጠው የሰዋሰው ትምህርት ዋነኛ አላማም የቋንቋ የመረዳትን ክሂሎት ማሳደግ ነው፡፡ የሰዋሰው ትምህርት የመረዳት ክሂል ሲጎለብት ለመግባቢያነት አገልግሎት ከመዋል ባለፈ ትምህርቶችን ለመማር፣ ለማወቅ፣ የረቀቀ አስተሳሰብን ለማጎልበትና ከአለም ህዝብ መረጃ ለማግኘት ትልቁን ድርሻ የሚይዝ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ (Algeo, 2006; Millar, 2015)፡፡

በመሆኑም አጥኚው ይህንን ጥናት እንዲያጠና ያነሳሳው ዋናው ምክንያት ቀደም ብሎ በጥናቱ ዳራ ለመግለጽ እንድተሞከረው በንድፈ ሀሳብ ደረጃ አንዳንዶች ሰዋሰው መማርያ ብልሃቶች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ችሎታን ለማዳበር አስፈላጊ መሆናቸውን አትኩሮት በመግለጻቸው ያለውን ልዩነት በጥበቱ ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል (Delilu, 2007; ወይንሸት ታደሰ, 2011)፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ የቀረቡት መረጃዎች የሚያረጋግጡት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ስርዓት (ሰዋስው) እየተማሩም ሆነ ተምረው ሲያበቁ የአጠቃቀምና የሰዋስው ችሎታ ችግር መስተዋሉን ነው፡፡ ስለዚህ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ የብልሃት አጠቃቀማቸውን መመርመር ያስፈልገናል፡፡

ስለ ሰዋሰው መማሪያ ብልሃቶች አጠቃቀም ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑና ለተማሪዎች የሰዋሰው እውቀት መዳበር ችግር ዋነኛ  ምክንያት የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ችግር እንዳለው በመገንዘቡ ይህንን ጥናት እንዳጠና አነሳስቷል፡፡ ምክንያቱም የመጽሃፍ መልመጃዎችና የአቀራረብ ዘዴዎች ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የሰዋሰው እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ የተለያዩ ማስተማሪያ ብልሃቶችን ከማስተዋወቅ ጋር የተያያዘ አይደሉም፡፡ (Allen & Valette, 1977; Harris, 1969)

Cook (2001) ስለ ሰዋሰው ምንነት ከመናገራቸው በፊት ሰዋሰው በተለያየ መንገድ እንደሚገለጽና እንደሚበየን ያስቀምጣሉ፡፡ ከእነዚህም አንዱ አዛዥ ሰዋሰው ሲሆን ‹‹ይህን በል፤ ይህን አትበል›› በሚል የቋንቋን ልማዳዊ ህግጋት መሠረት አድርጎ እንደተበየነ ያስቀምጣሉ፡፡ ከዚህ ሌላኛው ደግሞ ሰዋሰው ጥንታዊ ሰዋሰው ወይም የትምህርት ቤት ሰዋሰው በማለት የሚፈረጅና የንግግር ክፍሎችን ለመለየት የሚያስችሉ ህጎችን የያዛ በማለት የሚወሰን መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ሰዋሰው ስለ ቋንቋ ክፍሎች ማለትም ስም፣ ቅጽል፣ ግስ፣ ተውሳካ ግስ እና መስተዋድድ አንዱ ከሌላ የሚለይበትን ባህርይ የሚያሳይ የትምህርት አቀራረብ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ ሰዋሰው የቋንቋ መዋቅርና ሥርዓት የተመሰረተ ነው፡፡ እናም ሰዋሰው ቃላት፣ ሐረጋት ተቀናጅተው ዐ.ነገርን እንደሚመሰርቱ መዋቅራቸውን ተነትኖ የሚያሳይ መሆኑን ያስረዳል፡፡ Lyons (1968) ሰዋሰው የቃላት ህብረትና አገባብ የሚያሳይ ክፍል ነው ብለው ገልጸዋሉ፡፡

ከላይ ያየናቸው ምሁራን ሰዋሰውን ከተግባሩ በመነሳት ለመግለጽ የሞከሩ ሲሆን በአሁን ወቅት ለትምህርት ተግባር የተዘጋጀ ትምህርት መሣሪያዎች ማለትም መርሀ ትምህርት፣ የተማሪውና የመምህሩ መጻህፍት ይዘቶች ሰዋሰውን እንደ አንድ ይዘት አካተው ቀርበዋል፡፡ ሆኖም ግን በተማሪዎች ላይ የሚታየው ሀሳብን በጽህፈትም ሆነ በንግግር መዋቅሩን በጠበቀ መልኩ የሚገልጽ አቅም በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል፡፡ በንግግርም ሆነ በጽህፈት ወቅት ተማሪዎቹ የሚመሠርቷቸው አረፍተ ነገሮች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ባለቤትና ማሳሪያ አንቀጹ የማይስማሙ ናቸው፡፡

ስለዚህ የዚህ ጥናት አጥኚ ተማሪዎች በ9ኛ ክፍል ውስጥ የክፍል ደረጃቸውን በሚመጥን መልኩ ሰዋሰዋዊ ስህተት የሌለበትን ዐ.ነገር መመስረት ያልቻሉበት ምክንያት የሰዋሰው ትምህርት የመማር ብልሃቶች ተገቢ ያለመሆን ችግር ይሆናል የሚል መለምት ይዟል፡፡ የሰዋሰው ትምህርት የመማር ብልሃቶች ትንተና ዙርያ ጥናት ለማካሄድ ተነስቷል፡፡ Cook.V. (2001)::

በተማሪዎች የሰዋስው የመማር ብልሃቶች ላይ ክፍተት መኖሩ የሰዋሰው ችሎታ ላይ አሉታዊ ተጽኖ እንዳለው የተለያዩ የምርምር ውጤቶች ቢያመላክቱም እስከአሁን ችግሩ ሊፈታ አለመቻሉ በሰዋሰው ትምህርት ላይ ያለው ጫና ከፍተኛ አድርጎ ቆይቶዋል፡፡ የሚስማሙ ምሁራን መኖራቸውን በመገንዘቡ፤ እነዚህ የሰዋስው ማስተማሪያ ብልሃቶች ላይ የተከናወኑት የምርምር ውጤቶች በጣም ውስንና ያሉትም እርስ በርሳቸው የምጋጩ መሆናቸው በማንሳት አጥኚው እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት አፋቸውን በከምባትኛ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋሰው ለመማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ለመተንተን ተነሳስትተዋል፡፡

## 1.3 ዋና ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስው ትምህርት ለመማር የሚጠቀሙባቸው የመማር ብልሃቶችን መለየትና መተንተን ሲሆን በዚህ ዋና ዓላማ ስር የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ቀርበዋል፡፡

- በከምባትኛ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስውን ሲማሩ፣ የሚጠቀሟቸው የመማሪያ ብልሃት አይነቶችን መለየት፣
- በከምባትኛ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስውን ሲማሩ ከቋንቋ መማር ብልሃቶች መካከል የትኞቹን አዘውትረው በመጠቀም ትምህርቱን እምደሚከታተሉ፣እንደሚጠቀሙና እንደማይጠቀሙ መለየት
- የሚከተሏቸው የሰዋስው ትምህርትን ለመማር የሚጠቀሙ የመማር ብልሃቶች በመለየት የመፍትሔ ሀሳብ መጠቆም

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት መከናወኑ ጠቀሜታ አለው ማለት “ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ጥናት አልተጠናም፡ ፡” ለማለት ተፈልጎ ሳሆን፣ በዘርፉም በስፋት መጠናት ያለበት መሆኑን ለመግለጽ ታስቦ ነው፡፡ ስለዚህም ሰዋስውን የመማር ብልሃቶች በሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች ላይ ትኩረት ያለመሰጠቱ ለችግሩ አሳሳቢነት የላቀ ድርሻ በመኖሩ ለጥናቱ አስፈላጊነት እንደመነሻ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አጥኚው ምልከታ ባደረገበት በእነዚህ ውስን ትምህርት ቤቶች ያለው ችግር፣ ከላይ ከተገለጸው ችግር ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም፤ ምናልባትም ጥናቱ ባሉት የ2ኛ ደረጃና ባሉት የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ችግሩ በስፋት እንደሚታይ አጥኚው በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ

በተግባር የተስተዋለ ነው። ስለዚህ በእነዚህ በተመረጡ ሦስት ውስን በሆኑት ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በመውሰድ ከብዙ በጥቂቱ የሰዋስው የመማር ብልሃቶችን መተንትን ጠቀሜታው የሰዋስው የመማር ብልሃቶችን ለመለያት ያስችላል፤ በሚል የመነሻ ሀሳብ ነው። ከዚህም የተነሳ የጥናቱ አስፈላጊነት ከተማሪዎች አንጻር፣ ለመምህራንና ለትምህርት ቤቶችም ጭምር ተመራጭነቱ አያጠራጥርም። ይኸውም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

- ከተማሪዎች አንጻር፡- ለተማሪዎች የሰዋስው የመማር ብልሃቶችን ለመለየት ያለ ስህተት አርመው ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ በመረዳት የትኛው ብልሃት እንደሚሻላቸው ለማገናዘብ ይረዳል።
- በሰዋስው ትምህርት አሰጣጥ ወቅት በቋንቋ የመማር ብልሃቶች ለሚያጋጥማቸው ተግዳሮቶች መፍትሔ ይጠቁማል።
- ለመምህራን፡- ይህ ጥናት የሌሎችን ተማሪዎች ችግሮች ለመፍታት፤ ጥናትና ምርምርም ማድረግ እንዲችሉ፣
- ለትምህርት ቤቶች፡- ከዚህ ተሞክሮ በመነሳት በሌሎች ትምህርት ቤቶችም ጥናቱን በስፋት ችግሩን ለመፍታት እንድያመች ታስቦ ነው።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በ2015 ዓ.ም በከምባታ ጠምባሮ ዞን በአንጋጫ ወረዳ ከሚገኙ 6 ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተመረጡ በሦስት 9ኛ ክፍል የሚማሩ በከምባትኛ አፈ-ፊት በሆኑ ተማሪዎች ላይ የሚገደብ ሲሆን፣ ይህም ሲታይ የሰዋሰው መማሪያ ብልሃቶች ላይ ያተኩራል። በከምባትኛ አፍ-ፊት ለሆኑ ተማሪዎች ለሰዋስው ችሎታ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ ላይ ያጠነጥናል። ይህም ጥናት ከሰዋሰው መማርያ ብልሃቶች መካከልም፡- በአእምሮአዊ፣ በልእለ አእምሮአዊ፣ በትውስታ እና በማህበራዊ ብልሃቶች አንጻር የተማሪዎቹን የመማር ብልሀቶች ላይ ያተኮረ ነው። ከእነዚህም በተጨማሪ ጥናቱ አካካሽ እና ስሜት ነኪ ብልሃቶችንም አካቷል። ከተጠኚ ተማሪዎች አንጻርም የከምባትኛ አፍ-ፊት እንጂ የአማርኛ አፍ-ፊት ተማሪዎችን አያካትትም።

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት የሚካሔደው በደብብ ክልል ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አንዱ በሆነው በአንጋጫ ወረዳ ነው። በመሆኑም በዞኑ ውስጥ ከሚገኙት የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርት ቤቶች (የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል) ከሚሰጥባቸው የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል ካለው

የክፍለ ጊዜ እጥረትና የገንዘብ አቅም ውስንነት በሶስት ትምህርት ቤቶች (ቀፀላማ፣ አንጋጫ እና ፉናሙራ) በ2015 ዓ.ም. 9ኛ ክፍል በሚማሩ አፋቸውን በከምባትኛ በፈቱ ተማሪዎች ላይ በመወሰኑ ጥናቱን አንጻራዊ በሆነ መንገድ ውስንነት እንዲታይበት አድርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የሰዋስው ትምህርት ምንነት

Rechards and Rodgers (1995:1) ከቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ከሚደረጉባቸው አበይት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ የሰዋስው ትምህርት ነው፡፡ ሰዋስውን የማስተማር ተግባር ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ቀዳሚነቱን ስናይ ጥንታዊ ከሚባል የግሪክ እና የላቲን ቋንቋዎች ትምህርት ውስጥ በሰፊው ተግባር ላይ ይውል እንደነበር ይገልፃሉ፡፡

ስለ ሰዋሰው ምንነት በርካታ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች ቢሰጡም እስከ አሁን ድረስ ቁርጥ ያለ ብያኔ አልተገኘለትም፡፡ እንደ Woods እና Batstone ለዚህም እንደምክንያት ሲያስቀምጡ ብዙ ሰዎች ስለሰዋሰው ያላቸው የተለያ የአመለካከት ነው በማለት ሀሳባቸውን ገልጸዋሉ (Batstone, 1994; Raimes, 1991; Woods, 1991)፡፡ እንደምሁራኑ ገለጻ ሰዋሰው በመጻፍ የምገኝ ስራት ነቅ፣ ሰዋሰው ከንግግር ይልቅ በጽሁፍ የሚገኝ ስርአት ነው፤ ሰዋሰው ትክክል ወይም ስህተት ማለት ነው የሚሉት ናቸው፡፡ በተጨማሪ የሰዋስውን ምንነት በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ ከሰጡት ምሁራን መካከል ጌታሁን (2011፤ XI)፡፡

> ሰዋስው ከቋንቋ ጥናቶች ውስጥ ስርዓትን የሚመለከት ክፍል ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ሰዋስው የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፊቺዎችን ይዞ ይገኛል፡፡ አንደኛው ፍቺ የሰው ልጅ የሚጠቀምበርትን ቋንቋ "እውቀት" የሚጠቀመውና በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ያለው ችሎታ ነው፡፡ የሰው ልጅ ቋንቋውን ሊያውቅና ሊጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስላለው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ሰዋስው አዕምሮዊ እሳቤ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋን ተመራማሪዎች ለቋንቋ ስርዓትና መዋቅር የሚያደርጉትን ገለጻ የሚጠቁመው ነው፡፡ ይህ ፊቺ የአንድን ቋንቋ ስርዓት ጥናት ስለሆነ ከመጀመሪያው ፍቺ ጠባብ ነው፡፡

ሰዋስው የቋንቋ ስርዓት መሆኑ ግንዛቤ ያገኘ ጉዳይ ይሁን እንጂ የአገባብ ስርዓቱ መሰረት በሚያደርጋቸው ተዋቃሪዎች ረገድ የግንዛቤ ልዩነቶችም ይታያሉ፡፡ በዚህ መሰረት ብዙዎቹ ብያኔዎች አረፍተነገርን መሰረት ያደረጉና ሰዋስው የቃላትን የቅንጅት ስርዓት የሚመለከት፣

በአረፍተ ነገር የሚታይና የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት መሰረት ያደረገ ቅደም ተከተላዊ የቃላት አገባብ ስርዓት መሆኑን Brown (1994) ይገልጻል። ከዚህ የተለየ መንገድ "የሰዋስው ትምህርት አንድን ቋንቋ ስርዓት ከድምጽ አሰካኩ እስከ ሀረግ አመሰራረት ድረስ የሚያሳይ መሆኑን ይህም ህግ በሚጣስበት ጊዜ ተግባቦት እክል እንደሚገጥመው የተረጋገጠ ነው" በማለት ባየ (2000፡XX) ሲያስረዱ፡ Ur (1988:4) በበኩላቸው ቃላት ወይም ቃል_አከል (bits of word) አሀዶች ተቀናጅተው ሰፊ ትርጉም ያለው የቋንቋ መዋቅር የሚፈጥሩበትና ቋንቋ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያደርግ ስርዓት ሰዋስው መሆኑን ያብራራል።

ይህን እንጂ የምሁራኑ ትርጓሜ መለያየት ሰዋስውን በመማርም ይሁን በማስተማር ሂደት የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሮ ማለፉ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ሰዋስው የቱንም ያህል አደናጋሪና አወዛጋቢ፣አዕምሮዊና ረቂቅ ቢሆንም ለትምህርትነት ከመቅረብ የገታው ነገር የለም። በ20ኛ ክፍለ ዘመን በ1925 እና በ1965 መካከል የስነ_ልሳን ምሁራን አቅጣጫውን ከመጀመሪያው ስነ_ድምጽ ጥናት ወደ ሁለተኛው የቋንቋ ጭብጥ ወደ ሰዋስው አድርገዋል (stern:1983 130_131)። ይህም የሰዋስው ጥናት እጅግ ውጤታማ የሆነበት፣እንዲሁም አወዛጋቢነቱም የተረጋገጠበት ነው። በጥንታዊያን የስነ_ልሳን ተመረማሪዎች አከፋፈል ሰዋስው ስነ_ምዕላድ እና ስነ አገባብ በማለት በሁለት እንደሚመደቡ ገልጸዋል። ቢሆንም ግን አከፋፈሉ ዘላቂ ሊሆን አልቻለም። ምክንያቱ ደግሞ የቾምስኪ ተወልደአዊ ንድፈ ሀሳብ የሰዋስውን ውስብስብ ባህርይ ግልጽ ሊያደርገው መቻሉ ነው።

በእርግጥ ቋንቋን የሚገለገል የሰው ልጅ ሁሉ በአከባቢው ከሚገኘው መረጃዎች ላይ ትርጉም የማግኘት፣ አረፍተ ነገር የመመሳረት፣ ሰዋስዋዊ ህጎችን የመረዳት እና ውስብስብ የቋንቋ ስርዓቶችን የመገንዘብ ተፈጥሮአዊ ተሰጥኦ አለው። ሆኖም ግን በማስተማርም ሆነ በመማር ጊዜ የቋንቋውን ስርዓት በመንገር፣በመተንተንና በማጥናት ብቻ የሚዳብር ሳይሆን ምልልሶችን አዘጋጅቶ ተማሪዎችን በማሳተፍ የተለያዩ መረጃዎችን በማሳየት በቀረቡት ይዘቶች ተማሪዎቹ ሀሳብ እንዲለዋወጡ፣ እንዲጠይቁ፣ እንዲመልሱ፣ እንዲወያዩና የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ መማርን በሚጠይቅ መንገድ ከሚዳብሩ እውቀቶች መካከል ሰዋስው አንዱ ነው (Harmer: 1988:12)። ሰዋስዋዊ ህጎችን የሚወስኑ አጠቃላይ መርሆች ለሁሉም ቋንቋዎች የጋራነት አላቸው። ሰዋስው አገባባዊ አካል፣ ስነ_ድምጻዊ አካል፣ፍቻዊ አካል እንደሚይዝ ይፋ ያደረጉት በ Stern (1983:141) የተጠቀሱት Chomsky (1957) ናቸው። በመሆኑም ሰዋስው ስነ ምዕላድና ስነ አገባብ ብቻ ሳይሆን ስነ ድምጻዊና ስነ ፍቻዊ አካል የሚጠናበት ሳይንስ ነው።

ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ የቋንቋን ትምህርት በሚከታተሉበት ጊዜ ከተግባቦት ክሂሎች በተጨማሪ ስርዓቱንም ይማራሉ። በአጠቃላይ ሰዋስው ከቋንቋ ድምጾች አፈጣጠር፣ከቃላት አመሰረራት፣ከሀረጋትና አረፍተ ነገር አወቃቀር፣ ከስነ ፍቺ፣ ከስነ አገባብና ከትርጉም ጋር የማይፈታ ውል ያለው የስነ ልሳን አካል መሆኑን ከዚህ በላይ ከቀረቡት ብያኔውችና ማብራሪያዎች መረዳት የሚቻል ይመስላል።

የሰዋስው ትምህርት የሚቀርበው ለአፍ ፈት ወይም ለኢአፍ_ፈት ተማሪዎች ሲሆን ይችላል። ስለዚህ ተማሪዎቹ በክፍል ደረጃው የቀረበላቸውን የሰዋስው ይዘት በውጤታማነት ለመማር የሚጠቀሙባቸውን ከቋንቋ መማር ብልሓቶች የትኞቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ መመርመሩ ተገቢነት ያለው ይሆናል።

## 2.2 የቋንቋን ሰዋስው የመማር ብልሃቶች

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ የጥናቱን ክለሳ ድርሳናት ማቅረብ ነው። ክለሳውም በሁለት ዓበይት ክፍሎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ክፍል ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶችን የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች ዳሰሳ የተከናወነበት ነው (Channell, 1988)።

በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የሰዋስው እውቀት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በዚህም ምክንያት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ለሰዋስው ትኩረት መሰጠት እንዳለበት ምሁራን በአንክሮ ይናገራሉ።

የመማር ብልሃቶች ጥናት የተጀመረው Aaron Carton የተባለው ምሁር እንደ እኤአ በ1966 ዓም ነው። "በውጪ ቋንቋ ጥናት ሀሳብ ፈልፍሎ የማውጣት (inferrnce) ዘዴ" በሚል ርዕስ ያቀረቡትን ጥናት ካሳተሙ በኃላ መሆኑን Rubin (1987:19) ይገልጻሉ።

በቋንቋ ለመግባባት ሰዋስው ጉልህ ሚና አለው፤ የሰው ልጅ በርካታ ዕውቀት ተከማችቶ የሚገኘው በሰዋስው ነው። ይህ ሲሆን ደግሞ በርካታ ስህተቶች ልፍጠሩ ይችላሉ፤ ከነዚህም አንዱ በአርፍተ ነገሮች ውስጥ የሚፍጠሩ ሰዋስዋዊ ችግሮች ናቸው። እነዚህን ችግሮች ለመለየት ደግሞ የተለያዩ ደረጃዎችን ማለፍ የግድ ነው፤ የድምፆች ቅንብር፣ የሆሄያቶች ቅንጅት የቃላትንና የሀረጋትን ውህደትና አንድነትን የሚጠይቅ ሰፊ ሥራ በመሆኑ ነው። የሰዋስው ዕውቀት በመማር-ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች እጅግ አስፈሊጊ ነው፤ ይህ እንድሆን ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ የሰዋስው ትምህርት መማርያ ብልሃቶችን መጠቀም የግድ አስፈላጊ ይሆናል።

ተመራማሪዎች የሰዋሰው ትምህርት ብልሃቶችን የበየኑት በተለያየ መንገድ ነው፡፡ ይህን ነጥብ አስመልክተው ስተሪን እንዳሉት የመማር ብልሃት በሁሉም ተመራማሪዎች ዘንድ በአንድ ዓይነት መንገድ ሲገለጽና አገልግሎት ላይ ሲውል አይስተዋልም፡፡ (Munoz, Gallardo and Alvarez, 2010) ሆኖም ግን የሰዋሰው የመማር ብልሃት የቋንቋ ተማሪዎች አገልግሎት ላይ የሚውል፣ አጠቃላይ ዝንባሌዎችን ወይንም ባህርያት የሚያካትት የአሠራር ዘዴ ነው፡፡ (Abstracting: Nguyen, 2008) እንደ ተመራማሪዎቹ እይታ ደግሞ የሰዋሰው መማር ብልሃት አንድ የ2ኛ ተማሪ ለመማሪ ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ባህርያት ናቸው፡፡ በ2ኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ሂደት የሰዋሰው መማር ብልሃቶች ጉልህ ጠቀሜታ አለው ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን ተማሪዎች ለመማር የሚፈልጉትን ሰዋስው ሁሉ ካለው ጊዜ፣ በእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎትና የሚማሩበት ዘዴ ወይም መንገድ የተለያየ ከመሆኑ የተነሰ በክፍል ውስጥ በማስተማር ብቻ የተማሪዎችን የሰዋሰው ክምችት ማዳበር አይችሉም (Mahdavi, 2014: S.Mahdavi, Rahnamayan, and Deb, 2018)::

የሰዋስው መማር ብልሃቶች ተማሪዎች አንድን ሀሳብ ለመረዳት፣ መረጃ ለማከማቸት፣ አዳዲስ መረጃ ለማግኘት፣ መማርን ለመቆጣጠርና ለመገምገም ወይም አንድን የተወሰነ ተግባር ለማከናወን የሚጠቀሙባቸው የተለዩ አስተሳሰቦች፣ እርምጃዎችና ስልቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም የቋንቋን ሰዋስው መማር ብልሃቶች በመማር ሂደት ውስጥ የአጭር ጊዜ የትውስታ ችሎታ ውስንነትን (limitation) ለማሻሻልና መረጃን ከአጭር ጊዜ ትውስታ ወደ ረጅም ጊዜ ትውስታ አሸጋግሮ ለመጠቀም በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ማለትም በአእምሯዊ የቋንቋን ሰዋስው መማር ንደፈ ሀሳብ እይታ የቋንቋ ሰዋስው መማር ብልሃቶች የቀረበውን መረጃ በመፈተሽ የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታን ለማሻሻል ሁነኛ መሳሪያ ናቸው:: (Hakan, Aydin, & Bulent, 2015; R. L. Oxford et al., 2014)

የቋንቋን ሰዋስው መማር ብልሃቶች የቃላትን፣ የንበትን፣ የሰዋስውን፣ የማንበብን፣ የማዳመጥን፣ የመናገርንና የመፃፍን ትምህርት ለማጎልበት የሚረዱ የተማሪዎች ልዩ የመማር መንገዶች ናቸው:: የቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ተሳትፎ ወቅት የሚያካሂዱትን ትምህርት በብዙ አቅጣጫ በመመልከት በራሳቸው ምርጫና በሚቀላቸው መንገድ እንዲማሩ የሚረዷቸው፣ በተለይ ደግሞ መምህሮቻቸውን ሁል ጊዜ ሊያገኙአቸው ስለማይችሉ ማንኛውንም ትምህርታዊ ተግባር በራሳቸው ሀይል እየሰሩ እንዲማሩ የሚያግዟቸው መንገዶች ናቸው፡፡ በተጨማርም እንዳስገነዘቡት ውጤታማ የቋንቋ

ተማሪዎች የትምህርታቸውን ሂደት የሚያደናቅፉ፣ የሚያሳዩትን ለውጥና መሻሻል የሚገቱ ችግሮችንና እንቅፋቶችን ለመቋቋምና ለትምህርታቸው ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በርካታ ብልሃቶች ይጠቀማሉ፡፡ በተጨማሪም በቋንቋ ሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ትኩረት የሚሰጡና ኃላፊነትን የሚቀበሉ፣ ሥራቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩና በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለመማር የሚሹ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥረቶች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ብቻ ሳይሆን ከጥገኝነት ተላቅቀው፣ በራሳቸው ጥረት እንዲማሩ ይረዷቸዋል (Azizi & Zamaniyan, 2013; Nikoopour, Salimian, Salimian, & Farsani, 2012; Zybert, 2005)፡፡

## 2.3 የቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሃቶች ክፍፍል/ምደባ

### 2.3.1 አእምሯዊ ብልሃቶች(cognitive strategies)

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው የተተኳሪውን ቋንቋ በቀጥታ አእምሮውን በመጠቀም ተረድቶና ከራሱም አፍልቆ በመለማመድ እንዲማር የሚያስችሉት ብልሃቶች ናቸው፡፡ ምሁራንም እንዳስገነዘቡት አእምሯዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ተተኳሪውን የቋንቋን ሰዋስው ሲማሩ በቀጥታ አእምሯቸውን በመጠቀም የሚተገብሯቸው የአሰራር መንገዶች፣ የሚወስዷቸው እርምጃዎች ወይም ችግር ማቅለያዎች ናቸው፡፡ ተማሪው በተተኳሪው ቋንቋ ቃላት ተግባራት ላይ በቀጥታ የሚጠቀምባቸው መሰረታዊ አእምሯዊ ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡ (Miller & Fox, 1994; Tılfarlıoğlu & Yalçın, 2005)

### 2.3.2 ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች

ልዕለ አእምሮታዊ (Meta-cognitive strategies)፡ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪዎች የሚማሩበትን የቋንቋ ይዘት በማቀድ፣ በመምራትና በምገምገም ለቋንቋ ትምህርት አተገባበር ሂደት የሚረዱዋቸው መንገዶች ናቸው፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች በልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች ስር የሚካተቱት ንዑሳን ክፍሎች ናቸው፡፡

ለቋንቋ ትምህርት ጽሞና መስጠት፡- የተማሪዎችን ስሜት ከሚረብሹና ሀሳባቸውን ከሚበትኑ ማነኛውም አላስፈላጊ ነገሮች ነጻ ሆነው የታላሚውን ቋንቋ ትምህርት በቀጥታ እንዲከታተሉ ለማድረግ የሚያስችሉ የመማር ብልሃቶች ናቸው፡፡

ኢላማ ተኮር መሆን፡- በቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚነገረውን ነገር ሁሉ ለመያዝ ከመልፋት ይልቅ ጠቃሚ የሚባሉት የትምህርት ይዘቶች ላይ በማነጣጠር ለመማሩ ትኩረት የመስጠት ብልሐቶች ናቸው፡፡

ራስ መር መሆን፡- ተተኳሪውን ቋንቋ ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ የሚያግዙ ክስተቶችን የሚፈጥሩባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ አጋጣሚዎች በቋንቋው የመግባባት ብቃታቸውን ማዳበር አለማዳበራቸውን ራሳቸው የሚገመግሙባቸው ብልሃቶች ራስ መር ብልሐቶች ይባላሉ፡፡

ችግርን መለየት፡- ለመማር ወይም ለለመደው ውጤታማነት የቋንቋ ትምህርቱ ዋና ዓላማ መታወቅ አለበት፡፡ ይህንን የቋንቋ ዓላማ ግብ ለማድረስ በሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ የሚገጥሙ ችግሮች ካሉ በመፈተሽና በማጥራት ልምምድና መፍትሔ የሚዘጋጁበት ብልሃት ነው፡፡

ራስን መቆጣጠር፡- በቋንቋ ትምህርት ሂደት ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስውና ቃላት መረዳታቸውን፣ የቋንቋውን ትምህርት ድምጾች ግንባታቸውን በትክክል መገንዘባቸውን፣ በቋንቋ ክህሎች (በማዳመጥ፣ በማንበብ፣ በመናገርና በመጻፍ) ለመጠቀም መቻላቸውን ወዘተ የሚመለከቱ ብልሃቶች ናቸው፡፡

ማደራጀት፡- ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች፣ወደፊት ሊማሩዋቸው የሚያስቧቸውን ይዘቶች በሚመለከት መረጃዎችን ቀድመው በመፈለግ የሚያዘጋጁበት ቅድመ ሁኔታ ብልሃቶች ናቸው፡፡

### 2.3.3 ማህበራዊ ብልሃቶች(social strategies)

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ከክፍል ጓደኞቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ማህበራዊ ተራክቦ በመፍጠር ሰዋስውን እንዲማር የሚረዱት ብልሃቶች ናቸው፡፡ ቋንቋን ለመማር የሌላ ሰው ተሳትፎ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ተማሪዎችም ለሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማነት በጋራ ሊሰሩ ይገባል፡፡ ስለሆነም ማህበራዊ የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተጋገዙ፣ ግልፅ ያልሆነላቸውን ወይም እርግጠኛ ያልሆኑበትን እንግዳ ነገር መምህራንን ወይም ሌሎች ሰዎችን እየጠየቁ እንዲማሩ የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ ማህበራዊ ብልሃቶች የሰዋስውን ችሎታን ከማዳበር በተጨማሪ ማህበራዊ ተቀባይነትንም ያሳድጋሉ በማለት ገልጸዋሉ O'malley እና Chamot, (1990)፡፡

### 2.3.4 አካካሽ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ደግሞ ተማሪዎች በሰዋስው ዕውቀት ማነስ ምክንያት በተግባቦት ሂደት የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመቋቋም የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ናቸው። እንዳስገነዘቡት አካካሽ ብልሃቶች የሰዋስው ዕውቀት ክምችት እጦትን ለማካካስ የሚረዱ ብልሃቶች ናቸው። ለትምህርት የበለጠ ተገቢነት ያለው አካካሽ ብልሃት የአዳዲስ ሰዋስው ከአውድ የመገመት ብልሃት ነው። እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ሁለት የተለያዩ ፍንጮችን (መረጃዎችን) ማለትም ስነልሳናዊ (በቋንቋው ያለንን እውቀት)ና ኢ-ስነልሳናዊ ፍንጮችን በመጠቀም የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመገመት የሚረዱት ናቸው (Al Abri, Al Seyabi, Al Humaidi, & Hasan, 2017)።

### 2.3.5 ትውስታ ብልሐቶች

እነዚህ ብልሃቶች ይህን ቋንቋ ተማሪዎች በአጭርና በረጅም የትውስታ ጓዳ ውስጥ ያጠረቀሟቸውን የቋንቋ እውቀቶች አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት አስታውሰው ለመጠቀም የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው። ይህ የማጠራቀም፣ የማብሰልሰልና መልሶ የመጠቀም ሁኔታ የሚኖረው የቋንቋ ተማሪው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወይም ከመማሪያ ክፍል ውጪ የመማር ልምምዱን በሚያከናውንበት ወቅት ነው።

### 2.3.6 ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች

ለቋንቋ ተማሪ ስኬታማነት ጥሩ ሚና ከሚጫወቱ የመማር ብልሃቶች ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ይጠቀሳሉ። የቋንቋ ተማሪው በተገቢው መንገድ ስሜቱን ተቆጣጥሮ መማር ከቻለ ውጤታማ ይሆናል። እነዚህ ብልሃቶች ሶስት ሲሆኑ ሲጋትን(ጭንቀትን) መቀነስ፣ራስን ማበርታትና ውስጣዊ የፍርሓት ግፊቶችን መቆጣጠር መቻል ናቸው (Oxford: 1990:140)። በቁንቋ ትምህርት ሂደት በተማሪው ላይ የሚከሰቱ ስሜቶችንና ዝንባሌዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እንዲሁም ለመማር መነቃቃትን የሚያበረታቱ ብልሃቶች ናቸው። እነዚህን ብልሃቶች በቋንቋ መማር ወቅት በተገቢው መንገድ መተግበር ያስፈልጋል (Oxford: 1990)።

## 2.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የቋንቋ መማር ብልሃቶችን ትኩረት በማድረግ ለሁለተኛ ድግሪ ሟሟያነት ጥናቶች ተሰርተዋል። እነዚህ ጥናቶች በአንድም ወይም በሌላ መንገድ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው። ከዚህ ቀጥሎ ቀደም ሲል የተሰሩት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚኖራቸውን

የርስ በርስ ግንኙነት፣ያስገኙትን ውጤትና ይህ ጥናት በበኩሉ ሊጨምር የሚችለውን እውቀት ለማሳየት ይሞክራል።

ይርጋ (1993) "አፋቸውን በከፊኛ የፈቱ "ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች" አማርኛን ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ቋንቋ የመማር ብልሃቶችና የመምህራን ግንዛቤ አሰሳ" በሚል ርዕስ የመመረቂያ ጽሑፋቸውን አቅርበዋል። የይርጋ ዓለም የጥናት ዓላማ እንደሚያመለክተው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ "ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች" ቋንቋ ሲማሩ ሚገለገሉባቸው ቋንቋ የመማር ብሓቶችና የቋንቋ መምህራን በእነዚህ የመማር ብልሃቶች ዙሪያ ያላቸውን የግንዛቤ ሁኔታ መመርመርና ማጥናት የሚል ነው። ይርጋ ዓለም ባደረጉት ጥናት ውጤት መሰረት ስድስቱም ዓይነት ዋና ዋና የቋንቋ መማር ብልሓቶች በጥቅም ላይ የሚውሉ መሆናቸውን አረጋግጠው ሴቶቹ የቋንቋ ተማሪዎች ከወንዶቹ የተሻሉ መሆናቸውን በጥናቱ አሳይተዋል። በተጨማሪም የቋንቋ መምህራኑ በተማሪዎቻቸው ቋንቋ መማር ብልሃቶች ዙሪያ ግንዛቤ የሌላቸው በመሆኑ በተማሪዎች የቋንቋ መማር ሂደት እና በመምህራኑ የቋንቋ የማስተማር አቀራረብ ሂደት አለመጣጣም ሊኖር እንደሚችል ጠቁመዋል።

ከላይ የቀረበው ጥናታዊ ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ጥናት የሚለየው "አፋቸውን በከፊኛ የፈቱ "ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች" አማርኛን ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ቋንቋ የመማር ብልሃቶችና የመምህራን ግንዛቤ አሰሳ" የሚመለከት መሆኑ ነው።

በመሆኑም ተማሪዎች በመምህራን ያማያገኙትን የእውቀት ክፍተት በራሳቸው የሚሞሉበት ብልሐት መጠቀም ግድ ሊላቸው ይችላል። ይህ ጥናት በከምባትኛ ኣፈቸውን የፈቱ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ሲማሩ የሚገለገሉባቸው መማር ብልሃቶች ትንተና በመሆኑ ከላይ በይርጋ ጥናት የታየውን ሰዋስውን በክፍል ውስጥ ለመተግበር የሚያስችሉ ብልሐቶች እጥረት በተማሪዎች የመማር ብልሐቶች ለመሙላት እድል ሊሰጥ ይችላል።

ከዚህ ባሻገር በላይነሽ (2002) ያቀረቡት የሁለተኛ ዲግሪ ሚሚያ ጽሁፍ "በኦሮሚያ ክልል በኤልባበር ዞን በመቱ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛን ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶች ፍተሻ" በሚል ርዕስ ስለመማር ብልሃቶችና የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪውችን የሚመለከት ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ጉዳይ ነው። የበላይነሽ ጥናት ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛን ቃላት ሲማሩ የሚገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶች የሚፈትሽ ነው። የበላይነሽ ጥናት ውጤት ያረጋገጠው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ

ቃላትን የሚማሩበት መንገድ የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት በቀላሉ ለመማር በተለየ መንገድ እገዛ የሚያደርጉ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በመጠቀም ላይ ሆኖ አለመገኘቱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ተማሪዎች የተተኳሪውን ቋንቋ አዳዲስ ቃላት በትውስታ፣ በስሜት ነኪ ቁጥጥር፣ በማህበራዊና በልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩበትን የአማርኛን ቋንቋ ቃላት የሚማሩባቸው ብልሃቶች ከላይ በበላይነሽ ጥናት እንደተመለከቱት ከሆነ፣ የአማርኛን ቋንቋ ሰዋስው ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ብልሃቶች የትኞቹ እንደሆኑ መለየቱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በከምባትኛ አፈቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ሰዋስው የመማሪያ ብልሐቶችን ለይቶ ለማሳየት ይሞክራል፡፡

የመማር ብልሃቶችን በሚመለከት የሁለተኛ ዲግሪ ሟሟያ ከተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች መካከል ሌላው በንጋቱ (2000) "በሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሃቶች ምርመራ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የንጋቱ ጥናት ዓላማ የነበረው በሲዳምኛ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ቃላት የመማር ብልሃቶች መመርመር ነው፡፡ የንጋቱ የጥናት ውጤት አብዛኞቹ የጥናቱ ተተኳሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አዳዲስ ቃላት በትውስታ፣በስሜት ነኪ ቁጥጥር፣ በማህበራዊና በልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች አልፎ አልፎ በመገልገል አሳይቷል፡፡ በንጋቱ (2000) ጥናትና በበላይነሽ (2002) ጥናት መካከል የውጤት ልዩነት ያለው አይመስልም፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ጥናቶች አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ የሚገለገሉባቸውን የመማር ብልሃቶች ለይተው ለማሳየት ችለዋል፡፡

ሌላው የመማር ብልሃቶችን በሚመለከት የሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ጽሑፍ ያቀረቡት አፈወርቅ (2008) "በጋሞጎፋ ዞን በምዕራብ አባያ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት አፍ ፈት እና ኢአፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው የቃላት መማር ብልሃቶች ትንተና" በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ የአፈወርቅ የጥናት ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ አፍ ፈት እና ኢአፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን ለመማር የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች መተንተን ነው፡፡ የአፈወርቅ የጥናት ውጤት

እንደሚያሳየው በርካታ ቃላት የመማር ብልሃቶችን የሚጠቀሙት ኢአፍ ፈት ተማሪዎች እንደሆኑ የጥናታቸው ውጤት አሳይቷል።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች የመጀመሪያው የጥናት ዓላማ እንደሚያመለክተው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ “ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች” ቋንቋ ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ቋንቋ የመማር ብልሃቶችና የቋንቋ መምህራን በእነዚህ የመማር ብልሃቶች ዙሪያ ያላቸውን የግንዛቤ ሁኔታ መመርመር እና ማጥናት የሚል ነው። ሁለተኛው የጥናት ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋችውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚገለገሉባቸው የአማርኛ ቃላት የመማር ብልሃቶች ፍተሻ ነው። ሦስተኛው የጥናት ዓላማ የነበረው በሲዳምኛ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚገለገሉባቸውን ቃላት የመማር ብልሃቶች መመርመር ነው። የመጨረሻው የጥናት ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ አፍ ፈት እና ኢአፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን ለመማር የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች መተንተን ነው።

በተጨማሪ በአፈወርቅ ይስሐቅ የተሠራው ጥናት በብልሃት ትንተና ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ሆኖ ለትምህርትነት በቀረበው ይዘትና በአማርኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎችንም የሚያካትት በመሆኑ ይለያል፡፡ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች በይዘት ወይም በፍተሻው ዘዴ ከዚህኛው ጥናት የሚለያዩ ስለሆነ ይህ ጥናት ወጥ ጥናት ነው ማለት ይቻላል፡፡

የዚህ ጥናት ዓላማ ደግሞ በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስውን ለመማር የሚጠቀሙባቸውን የቋንቋ የመማሪያ ብልሃቶች መተንተን በመሆኑ፣ልዩነት አላቸው። የሚመሳሰሉበት ነገር ቢኖር ደግሞ ሁሉም ጥናቶች በመማር ብልሃቶች ለሚነሱ ጉዳዮች ፍንጭ የሚሰጡ መሆናቸው ነው።

ይህ ጥናትም ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች ጋር በመደመር በምሁራን ተለይተው ከተቀመጡት ስድስት (የትውስታ ብልሃቶች፣ አካከሽ ብልሃቶች፣ አዕምሮታዊ ብልሃቶች፣ ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች፣ ማሕበራዊ ብልሃቶችና ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች) ቋንቋን የመማር ብልሃቶች መካከል የሰዋስው ትምህርትን ለመማር የሚያገለግሉትን ብልሃቶች በመተንተን ለመሳየት ጥረት አድርጓል።

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት በአይነቱ መጠናዊ ምርምር (Quantitative Research)። መረጃውም በጽሁፍ መጠይቅ፣ በቃለመጠይቅና አማካኝነት ከመምህራን፣ ከተማሪዎች ተሰብስቦ በገላጭ (Descriptive) የትንተና ስልት ተተንትኗል። የጽሑፍ መጠይቁ ትምህርት ቤት ለሚገኙ አፋቸውን በከምባትኛ ለፈቱት ተማሪዎች ብቻ ተበትኗል። የጽሑፍ መጠይቁን የሚሞሉት ተማሪዎች የተመረጡት የጥናቱ ተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚካሄደባቸው የመማሪያ ክፍሎች አንድ ሦስተኛው (35%) የሚሆኑ ተማሪዎችን ከየክፍሉ በናሙናነት በመውሰድ ተካሄዷል። ከጽሑፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅም የዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል። በመሆኑም ጥናቱ ገላጭ የምርምር ንድፍን በመጠቀም የተማሪዎችን የመማር ብልሃቶች አጠቃቀም ለመተንተን ጥረት ተደርጓል። ገላጭ የምርምር ስልት የተመረጠበት ምክንያት ተመራማሪው አንድ ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚቀበልበት በመሆኑ ነው።

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ

በትምህርት ቤቶች የናሙና አመራረጥ ረገድ በጥናቱ በአንጋጫ ወረዳ ካሉት ስድስት ሁለተኛ ደረጃ የመጀመርያ እርከን ትምህርት ቤቶች ቢገኙም ከጉልበት፣ ከገንዘብና ከጊዜ ውስንነት አንጻር ለአጥኚው የስራ አከባቢ ቅርብ የሆኑትን ቀዕላማ፣ አንጋጫ እና ፉናሙራ ትምህርት ቤቶች በአማቺ የናሙና አመራረጥ የጥናቱ ወካይ ትምህርት ቤቶች እንዲሆኑ ተማርጠዋል። በእነዚህ ሶስት ትምህር ትምህርት ቤቶች ውስጥም አፋቸውን በከምባትኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ሰዋሰውን ለማመር የሚጠቀሙባቸው የቋንቋ የመማር ብልሃቶች ክፍተቱ ይኖራቸዋል ብሎ በማመኑ ነው።

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ_10ኛ ክፍል)ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርትን በሚመለከት ከመጀመሪያ ደረጃ (1_8ኛ ክፍል) ተማሪዎች ይልቅ የተሻለ ግንዛቤ ይኖራቸዋል በማለት በእኩል የእድል ሰጭ የእጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ከሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ተማሪዎች መካከልምርጫው ተካሄዷል።በተከናወነው የእጣ ማውጣት ሂደትም ዘጠነኛ የክፍል ደረጃ ለጥናቱ ተመራጭ ሆነው ቀሪዎቹ ተማሪዎች 10ኛ ክፍል ዕጣው ስላልወጣለት በጥናቱ አልተካተቱም።

### 3.2.3. የተማሪዎች አመራረጥ

የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ በሚመለከት ከጥናቱ ዓላማ አንጻር በከምባትኛ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው መኖራቸው ተረጋግጧል። በመሆኑም ከቀዕላማ በአንድ ሴክሽን ከሚማሩ 63 ተማሪዎች መካከል 21 ተማሪዎች፣ ከአንጋጫ 2ኛ ደረጃ በ3 ሴክሽን ከሚማሩ 153 ተማሪዎች ከእያንዳንዱ ሴክሽን 17 በመውሰድ በአጠቃላይ 51 ተማሪዎች እና ከፉናሙራ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2 ሴክሽን ከሚማሩ 102 ተማሪዎች 34 ተማሪዎች የተመረጡ ሲሆን በጠቅላላው ከሦስቱም ትምህርት ቤቶች106 ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል። ከሦስቱም ትምህርት ቤት ተማሪዎች በቀላል እጣ ናሙና (Simple Random Sampling) ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ተማሪዎች በመማር ክንውን ጊዜ የተለያዩ ችግሮችን እየፈቱ ሲማሩ የትኛው የቋንቋ መማር ብልሃት ለየትኛው ችግር መፍቻነት እና ለየትኛው ክንውን መተግበሪያነት እንደሚውል አስታውሰው ለመመለስ እድል የሚሰጠው የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያ የጽሑፍ መጠይቅ ነው።ይሁን እንጂ ለዚህ ጥናትአስፈላጊ ሆኖ የተገኘው የመረጃ መሰብሰቢያ የጽሑፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው። የጽሑፍ መጠይቅ በዋናነት፣ ቃለ መጠይቅ ደግሞ በአጋዥነት ስራ ላይ ውለዋል።

### 3.3.1 የጽሑፍ መጠይቅ

አንደኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሰዋስው መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ነው። የጽሑፍ መጠይቁ ከሌሎች ከዚህ በፊት ከተጠኑና ከታተሙት

መጠይቆች ለዚህ ጥናት እንዲስማማ መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ የሚዘጋጁና በስድስቱ ዋና ዋና የሰዋስው መማር ብልሃቶች (በትውስታ፣ በአካካሽ፣ በአዕምሯዊ፣ በልዕለ አዕምሯዊ፣ በማህበራዊና በስሜት ነኪ ቁጥጥር የሰዋሰው መማር ብልሃት) ስር የሚመደቡ፣ ብልሃቶችን መሰረት ያደረጉ ናቸው።

የጽሑፍ መጠይቁን ተገቢነትና አስተማማኝነት ለመፈተሽ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት የጥናቱ አማካሪ፣ ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ ክፍል በሚያስተምሩ አንደኛ ዲግሪ ያላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ያላቸው መምህራን እንዲያዩትና እንዲገመግሙት ተደርጓል። ከመምህራኑ እና ከጥናቱ አማካሪ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግም መጨመር ያለባቸው ተጨምረዋል፣ መሻሻል ያለባቸው ተሻሽለዋል፣ መወገድ ያለበቸው ተወግደዋል፣ የአሻሚነት ባህሪ የሚታይባቸው በማብራራት ግልጽ የማድረግ ተግባራት ተከናውነዋል፤(ለምሳሌ፡- የአጠያየቅ ችግር ያለባቸው ጥያቄዎች ማስተካከል)። የዘርፉ ባለሙያዎችን ግምገማና አስተያየት መሰረት በማድረግም የጽሑፍ መጠይቁን ተገቢነት (validity) ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል። ከዘርፉ ባለሙያዎች ሙያዊ ግምገማና አስተያየት በኋላም የጽሑፍ መጠይቁን አስተማማኝነት (Reliability) ለማረጋገጥ የአስተማማኝነት መገመቻ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል። በዋናው ጥናት የሰዋስው መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቆቹን የአስተማማኝነት ደረጃ ለመወሰን ተግባራዊ ሆኗል።

### 3.3.2. ቃለ መጠይቅ

የቃለ መጠይቁ ዓላማ በጽሑፍ የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥና ተጠኚዎቹ ስለመማር ልምዳቸው አስመልክተው በሚሰጡት ማብራርያ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሰዋስው የመማር ብልሃቶች መሰረት ያደረጉ 10 ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ከሦስቱም ትምህርት ቤቶች የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉት ተጠኚዎች መካከል በተመጣጣኝ ናሙና ዘዴ ከቀዕላማ2፣ ከአንጋጫ 7 እና ከፉናሙራ 3 ተማሪዎች በአጠቃላይ 12 ተማሪዎች በዕጣ ተመርጠው ቃለ መጠይቁ ተካሔዷል።

## 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህጥናት መሰረታዊ ዓላማው በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በአንጋጫ ወረዳ ካሉት 6 ትምህርት ቤቶች ወስጥ በተመረጡ ሦስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሰዋስው ለመማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችን መተንተን ነው። በመሆኑም ስለመማር ብልሃቶች ያላቸውን ዕውቀትና ልምድ፣ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ፣ ሰዋስውን

ለመማር የሚጠቀሙባቸው ከስድስቱ የመማር ብልሃቶች የትኞቹን ለአማርኛ ሰዋስው መማር እንደሚገለገሉባቸው ለመለየትና ደረጃ ለማውጣት ተሞክሯል፡፡

በመሆኑም በመጀመሪያ በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን ለመለየትና የጽሑፍ መጠይቁን በትክክል መሙላታቸውን ለማረጋገጥ ቅድመ ትንተና እና ፍተሻ ተከናውኗል፡፡ የሰዋስው መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቁን የማያሟሉ በጥናቱ እንዳይካተቱ ተደርጓል፡፡ በጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች የትንተና ውጤት ምን እንደሚመስል ለማየት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት በጽሑፍ መጠይቁ የቀረቡ ብልሃቶች አእምሮታዊ (1 እስከ 14 የተዘረዘሩት መጠይቆች)፣ ማህደረ ትውስታ (15 እስከ 23 የተዘረዘሩት መጠይቆች)፣ አካካሽ (ከ24 እስከ 27 የተዘረዘሩት መጠይቆች)፣ ልዕለ አዕምሮታዊ (ከ 28 እስከ 33 የተዘረዘሩት መጠይቆች) ስሜት ነኪ ቁጥጥር (34 እስከ 37 የተዘረዘሩት መጠይቆች) እና በማህበራዊ (38 እስከ 42 የተዘረዘሩት መጠይቆች) አማካይነት የሚገኙ መረጃዎችን በቁጥርና በመቶኛ ተጠቃለው እንዲታዩ በማድረግ አይነታዊ (qualitative) የትንተና ዘዴን በዋናነት እንዲሁም አሃዛዊ (quantitative) የትንተና ዘዴን በአጋዥነት በመጠቀም በቃለ-መጠይቁ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር እየተደጋገፉ እንዲተነተኑ ተደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና እና ውጤት

ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ርቱዕና ኢርቱዕ ተብለው በሁለት ዋና ዋና አብይ ምድቦች ይከፈላሉ። እነዚህም ዋና ዋና የመማር ብልሃቶች በስራቸው ሶስት ሶስት ንዑሳን ብልሃቶችንና ሌሎች ዝርዝር ብልሃቶችን እንደሚያካትቱ ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ለማሳየት ተሞክሯል። በመሆኑም ተጠኚ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው የሚማሩበት ሁኔታ የትኞቹን ብልሃቶች መሰረት እንደሚያደርጉ ለመመርመር የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተል ይቀርባሉ።

## 4.1የርቱዕ መማር ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

ቋንቋን ለመማር ተገቢ የሆኑ ርቱዕ ብልሃቶች ተብለው የሚታወቁት ንዑሳን ብልሃቶች አእምሮታዊ፤ ትውስታና አካካሽ በመባል የቀረቡት ናቸው። ቋንቋን በነዚህ ብልሃቶች መማር የታላሚውን ቋንቋ ልዩልዩ ተግባራት በቀጥታ እያከናወኑ ቋንቋውን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ እንዲማሩ የሚያገለግሏቸው ብልሃቶች ናቸው። ከዚህ በማስከተል የእያንዳንዱን ብልሃት መረጃ ትንተናና ውጤት በዝርዝር ይመለከታል።

### 4.1.1 የአእምሮታዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

ከተራ ቁጥር 1-5 የተዘረዘሩት የጽሁፍ መጠይቆች ተማሪዎች ስለ አእምሮታዊ ብልሃቶች ያላቸውን አጠቃቀም ልምድና እውቀት ለመተንተን የቀረቡ ናቸው።

በድርሳን ክለሳው እንደተጠቆመው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ስለሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ድንገት ቢጠየቁ የትኞቹን እየተገለገሉ ትምህርታቸውን እንደሚከታተሉ ምላሽ መስጠት ይችላሉ (Rubin, 1987)፡ ፡

ከዚህ ቀጥሎ ከሰንጠረዥ አንድ በኋላ በሚመጡት ገጾች የእያንዳንዱ መጠይቅ ዝርዝር ትንተናና ውጤት በተራ ቁጥራቸው መሰረት ቀርበው ከዳር ሳንክለሳው ካሉ ትውረቶች ጋር በንጽጽር እየተገናዘቡ ቀርበዋል።

*ሠንጠረዥ 1 የአእምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ*

| ተ.ቁ | ብልሃቶች | የተዘዋታሪነት አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፍጹም | | አልፎ አልፎ ብቻ | | በአብዛኛው | | ሁል ጊዜ | |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| 1. | የሰዋሰው ይዘቶችን ከቀዳሚው የሰዋስው እውቀቱ ጋር በማስተሳሰር መማር | 63 | 59 | 13 | 12 | 18 | 17 | 12 | 11 |
| 2. | በዓይነት ዓይነት ድምጾችን፣ ቃላትን በማቧደንና በማመሳሰል መማር | 67 | 63 | 19 | 18 | 14 | 13 | 6 | 7 |
| 3. | የአማርኛ የቃል ክፍሎቻቸውን ማጥናት | 61 | 58 | 21 | 20 | 13 | 12 | 11 | 10 |
| 4. | በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ገለጻና ማብራርያ | 58 | 55 | 6 | 6 | 24 | 23 | 18 | 17 |
| 5. | ሰዋስዋዊ ፍሬ ነገሮችን ማስተወሻ መያዝ | 61 | 58 | 5 | 5 | 27 | 25 | 13 | 12 |
| | አማካይ | 62 | 59 | 13 | 12 | 19 | 18 | 12 | 11 |

ጥያቄ 1 ተማሪዎች አዳዲስ የሰዋስው ይዘቶችን ሲማሩ ቀደም ሲል በተማሯቸው የክፍል ደረጃዎች የሚያውቋቸውን በማስተሳሰር ስለ መሆኑ ተጠይቀዋል። ይህንን የመማር ብልሃቶች ፍጹም የማይጠቀሙ 63(59%) ያህል ተማሪዎች ሲሆኑ፣በሌላ መልኩ ይህን የመማር ብልሃት በአብዛኛው እንጠቀምባታለን ያሉት 18 (17%)ተማሪዎች ሆነው ተገኝተዋል። አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ 13 (12%) ያህሉ ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ብልሃቱን ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ሲሉ ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ቁጥር 12 (11%) ሆኖ ተገኝተዋል።

ጥያቄ 2 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹን በዓይነት ዓይነታቸው በማቧደንና በማደራጀት ይማሩ እንደሆነ ለማወቅ ሀሳብ ቀርቦላቸዋል። ይንን የመማር ብልሃቶች ፍጹም የማይጠቀሙ ተማሪዎች ቁጥር 67 (63%) ያህል ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ደግሞ 19 (18%)

ናቸው:: በአንጻሩ በዚህ ብልሃት በአብዛኛው የሚጠቀሙበት 14 (13%) ተማሪዎች መሆናቸውን መረጃው ሲያመለክት፣ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት 6 (6%) ያህል ተማሪዎች ናቸው::

ከቀረበው መረጃ ማረጋገጥ የሚቻላው፣ የማቧደን ብልሃቱን 63% ተማሪዎች የሚጠቀሙበት ቢሆንም እነ O' Malley (1990) የማቧደን ብልሃት ሰዋስውን ለመማር ከሚያገለግሉ አእምሮታዊ ብልሃቶች ዋናው መሆኑን ይገልጻል:: ስለሆነም ተማሪዎች የማይጠቀሙበት ምክንያት በክፍል ውስጥ የመምህራን ማበረታቻ አንስተኛ ሊሆን ይችላል (O'Malley, 1987)::

ጥያቄ 3 የአማርኛ ቃላትን በቃል ክፍሎቻቸው ለማጥናት የሚያስችል ብልሃት መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ የቀረበ ሀሳብ ነው:: የአንድን ቋንቋ የቃል ክፍሎች ማጥናት ከሰዋስው ትምህርት ይዘት መካከል አንዱ መሆኑ ይታወቃል:: በመሆኑም ጭራሽ አንጠቀምም ያሉት 61 (58%) ተማሪዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ ይህንን ብልሃት የሚጠቀሙ 21 (20%) ተማሪዎች ናቸው:: በኣብዛኛው ይህንን ብልሃት የሚጠቀሙ 13 (12%) ያህል ተማሪዎች ሲሆኑ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ 11 (10%) ተጠኚዎች ናቸው::

በዚህ መጠይቅ የሚታየው ውጤት የተማሪዎች የአጠቃቀም ተዘውታሪነት ደረጃ ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል:: የተማሪዎቹ ምላሽ በምሁራን አመለካከት የሚደገፍ ሆኖ አልተገኘም:: የአማርኛ ቋንቋ ድምጾች፣ ምዕላዶች፣ ሀረጋትና አረፍተ ነገሮችን ለማጥናት ምደባ ማድረግ አስፈላጊ ነው (ጌታውን 1990፤ III) (ባየ 2009፤ XXI):: የቃላት ምደባ በክፍል ደረጃ በሚመጥን መልኩ መማር ውጤታማ ያደርጋል:: ስለዚህ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ሰዋስዋዊ ትምህርት ከመከታተል አንጻር ችግር ሊኖር እንደሚችል መረጃው ያመለክታል::

ጥያቄ 4 ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተደጋጋሚ ገለጻና ማብራሪያ እንደሆነ ለመፈተሽ ተጠይቀዋል:: ከላይ በቀረበው የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ሰንጠርዥ እንደሚታየው ፍጹም የማይጠቀሙበት 58 (55%) ተጠኚዎች ሲሆኑ፣ በኣብዛኛው በማለት የመለሱ 24 (23%) ተማሪዎችናቸው:: ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት ተማሪዎች 18 (17%) ተጠኚዎች ሲሆኑ፣አልፎ አልፎ በማለት የመለሱ 6 (6%) ያህል ተማሪዎችናቸው:: በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት በመማር ብልሃት ባለሙያዎች በነ O' Malley (1990) እና Oxford 1990 የቀረቡትን ውጤታማ የመማር ብልሃቶች መሰረት ያደረገ አይደለም (Batstone, 1994; O'Malley, 1987; Oxford, 1990)::

ጥያቄ 5 አዳዲስ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ጊዜ ማስታወሻ በመጻፍ ትምህርታቸውን ይከታተሉ እንደሆነ ለማረጋገጥ የቀረበ መጠይቅ ነው፡፡ ፍጹም የማይጠቀሙበት 61 (58%) ተጠኚዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ የሚገለገሉበት 5 (5%) ያህል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ ብልሃት በአብዛኛው የሚማሩ 27 (25%) ተማሪዎች ሲሆኑ በሌላ በኩል ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት ተማሪዎች 13 (12%) ተጠኚዎች ናቸው፡፡ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም በምዕራፍ ሁለት ከተጠቀሱት የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ሚና ጋር የሚጣረስ ሆኖ ይታያል፡፡ Oxford 1990 እንደሚያስረዱት የቋንቋ ትምህርቱን ፍሬ ነገሮች፣ ክሂሎችን፣ ሰዋስውን፣ ቃላትን ወዘተ ዋና ወይም ዝርዝር ሀሳቦችን ጨምቆ ወይም አስፋፍቶ በቃል ወይም በጽሁፍ ለመያዝ ማስታወሻ የማያዝ ብልሃት ወሳኝ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች አማርኛን ለመማር የሚጀምሩት ከሶስተኛ ክፍል በመሆኑ የመጻፍ ክሂል እጥረት ሊኖርባቸው እንደሚችል የአጥኚው ግምት አለ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቀረበላቸው መጠይቅ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ መሆኑ (በከምባትኛ ቋንቋ ተተርጉሞ አለመቅረቡ) አንብበው ለመመለስ ችግር ገጥሟቸው ሊሆን ይችላል (Oxford, 1990)፡፡

በጽሑፍ መጠየቅ ውስጥ ከተራ ቁጥር 6-10 የቀረቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ስለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች የነበራቸውን ችሎታና የአጠቃቀም ደረጃ ለመተንተን ቀርበዋል፡፡ በመጠይቆቹም ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ 2 ተደራጅተው የቀረቡ መሆኑን የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

*ሠንጠረዥ 2 የአእምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ*

| ተ.ቁ | ብልሃቶች | የተዘዋታሪነት አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፍጹም | | አልፎ አልፎ ብቻ | | በአብዛኛው | | ሁል ጊዜ | |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| 6. | የአማርኛ ሰዋሰውን ከአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ጋር ማወዳደር | 60 | 57 | 7 | 7 | 29 | 27 | 10 | 9 |
| 7. | ከምባትኛ ቋንቋን በመጠቀም ሰዋስውን ለመማር | 74 | 70 | 11 | 10 | 7 | 7 | 14 | 13 |
| 8. | ድምጾችን፣ ቃላትንና ምዕላዶችን መተንተን | 68 | 64 | 8 | 8 | 22 | 21 | 8 | 8 |
| 9. | የሰዋሰዋዊ ልምምድን ማጠናከር | 10 | 9 | 34 | 32 | 47 | 44 | 15 | 14 |
| 10. | መልመጃዎችን በመስራት መማር | 11 | 10 | 36 | 34 | 43 | 41 | 16 | 15 |
| | አማካይ | 45 | 42 | 19 | 18 | 30 | 28 | 13 | 12 |

ጥያቄ 6 ተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን አፍ ከፈቱ በከምባትኛ ቋንቋ ሰዋስው ጋር በማዛመድ ለመማር የሚያስችል ብልሃት ስለመጠቀማቸው ለማወቅ ሀሳብ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ ይህንን የመማር ብልሃት ፍጹም አንጠቀምበትም ብለው የመለሱት 60 (57%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ በአብዛኛው የሚጠቀሙ ተማሪዎች 27 (27%) ያህል ናቸው፡፡ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት ደግሞ 10 (9%) ተጠኚዎች ሲሆኑ፣በአንጻሩ አልፎ አልፎ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ሰዋስው ከአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ጋር በማነጻጸር የሚማሩ 7 (7%) ያህል መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡

ከዚህ የትንተና ውጤት መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎች በብልሃቱ አለመጠቀማቸውን ነው፡፡ ነገር ግን የከምባትኛ ሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቋንቋቸውን ተደጋጋፍነት " ሰዋስዋዊ ህጎችን አጠቃላይ መርሆች ለሁሉም ቋንቋዎች የጋራነት አላቸው፡፡" የሚለውን Stern (1983፡

141) የተጠቀሱት የChomsky (1957)ን ሀሳብ መሰረት በማድረግ እንድጠቀሙበት ያለማድረግ ችግር ልኖር ይችላል (Sternn, 1983)።

ጥያቄ 7 የአማርኛ ሰዋስው ለመማር በከምባትኛ ቋንቋ የሚያውቁት ሰዋስው እረድቷቸው እንደሆነ ተጠይቀዋል። ጭራሽ እንደማይጠቀሙበት 74 (70%) ያህል ተጠኚዎች መረጃ የሰጡ ሲሆን፣ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት ተማሪዎች 14 (13%) ያህል ተማሪዎች ናቸው። አልፎ አልፎ ሲሉ ምላሽ የሰጡት 11(10%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ በአንጻሩ በኣብዛኛው የሚለውን አማራጭ የመረጡት 7 (7%)ተጠኚዎች ናቸው።

የአፍ መፍቻ ቋንቋ መዋቅርን ከታላሚው ቋንቋ መዋቅር ጋር በማነጻጸር መማር (Oxford 1990) ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ቢገልጹም ብልሃቱን 70% ተማሪዎች እንደማይገለገሉበት መረጃው ያረጋግጣል (Oxford, 1990)።

ጥያቄ 8 የአማርኛ ቋንቋ የሰዋሰው ይዘቶችን በከምባትኛ ቋንቋ ተጠቅመው በቃላቸው በመያዝ ወይም በመሸምደድ የመማር ልምዳቸውን ለመመርመር ሀሳብ ቀርቧል። በዚህ የመማር ብልሃት ፍጹም አንጠቀምበትም ያሉት ተማሪዎች 68 (64%) ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙበት 8 (8%) ያህል ተማሪዎች ናቸው። ከዚህ ባሻገር በኣብዛኛው እንጠቀማለን በማለት 22 (21%) ምላሽ ሲሰጡ፣ ሁል ጊዜ የሚለውን አማራጭ የመለሱ 8 (8%) ተማሪዎች ናቸው። ከላይ ከቀረበው መረጃ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በመጠቀም በቃላቸው በመያዝ ለመማር የሚያስችላቸውን ብልሃት ምንም የማይጠቅም አድርገው እንደሚመለከቱት መገንዘብ ይቻላል። ሆኖም ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትልቅ ሚና ያለው መሆኑን ነው Stren (1983)። ነገር ግን ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርታቸው በከምባትኛ ምንም ፊይዳ እንደሌለው አድርገው መውሰዳቸውን የሚያረጋግጥ ነው (Sternn, 1983)።

ጥያቄ 9 ከምባትኛ አፍ_ፊት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ሲያጠኑ ከፍተኛ ድግግም ያለው አሰራርን ስለ መከተላቸው ያላቸውን ልምድ ለመፈተሽ የቀረበ ሀሳብ ነው። በመሆኑም በኣብዛኛው የሚጠቀሙበት ተማሪዎች 47 (44%) ሲሆኑ፣አልፎ አልፎ የሚጠቀሙበት 34 (32%) ናቸው። ሁልጊዜ የሚጠቀሙበት 15 (14%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ይህንን ብልሃት በጭራሽ የማይጠቀሙበት 10 (9%) ተጠኚዎች ናቸው። ከዚህ በላይ በቀረበው መረጃ መሰረት ሰዋስውን ለመማር የሚጠቀሙበት ብልሃት ድግግም መሆኑን ኣብዛኞቹ ተማሪዎች

ሲያረጋግጡ Oxford (1990;45) አንድን የሰዋስው ይዘት ደጋግመው መማር ውጤታማ የማድረግ ብልሃት መሆኑን ከገለጹት ይርጋ (1997) ጥናት ውጤት ሀሳብ ጋር የተማሪዎቹ ምላሽ ስሙም ነው (Oxford, 1990; ይርጋ, 1997)፡፡

ጥያቄ 10 ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሰዋስው መልመጃዎችን የመስራት ብልሃት ለመፈተሽ ከቀረቡት አማራጮች በፍጹም የማይጠቀሙበት 11 (10%) ተማሪዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ 36 (34%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ በአብዛኛው በማለት 43 (31%) ተጠኚዎች ሲመልሱ፣ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት 16 (15%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ በክፍት መጠይቁ ሰዋስውን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ሌሎች ብልሃቶች ካሏቸው ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ የሌለ ቢሆንም የሚጠቀሙባቸው ቋንቋን ለመማር፣ በመተጋገዝ፣ የአማርኛን ቃላት፣ ድምጾች እንድንማር ያግዛሉ በማለት ምላሽ የሰጡ 7 ተማሪዎች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ከማህበራዊ ብልሃቶች የሚያያዙ ብልሃቶች መሆናቸውን የሚጠቁም እንጂ ከአዕምሮታዊ ብልሃቶች ጋር የሚገናኙ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በማህበራዊ ብልሃቶች ቅርበት ያላቸው መሆናቸውን የሚያሳይ ይመስላል፡፡ ተጠኚዎቹ የሰጡትን ምላሽ ለማረጋገጥ 12 ተማሪዎች ተመሳሳይ ቃለ መጠይቅ ተጠይቀዋል፡፡ የሰጡትም ምላሽ ከጽሑፍ መጠይቁ ከተገኘው መረጃ ጋር ስሙም ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከተራ ቁጥር 11-14 በጽሑፍ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች የአዕምሮታዊ ብልሃቶች መሠረት በማድረግ ታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው በአዕምሮአቸው ይዘው መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለመተንተን የቀረቡ ሲሆን ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን በአንድ ላይ በመቧደን ለተጠኚ ተማሪዎች ቀርበዋል፡፡ በአዕምሮታዊ ብልሃቶች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ ከታች ባለው ሳንጠረዥ ሦስት ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 3 የአእምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ*

| ተ.ቁ | ብልሃቶች | የተዘዋታሪነት አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፍጹም | | አልፎ አልፎ ብቻ | | በአብዛኛው | | ሁል ጊዜ | |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| 11. | ሰዋስውን ለመማር ለመረዳት ስዕሎችን መጠቀም | 55 | 52 | 11 | 10 | 24 | 23 | 16 | 15 |
| 12. | ሰዋስዋዊ ፍሬ ነገሮችን ለመለየት ማቅለምን መጠቀም | 64 | 60 | 20 | 19 | 15 | 14 | 7 | 7 |
| 13. | ግራፎችንና ሰንጠረዦችን መጠቀም | 60 | 57 | 21 | 20 | 11 | 10 | 14 | 13 |
| 14. | የእርማት ማስተካካዎችን መጠቀም | 56 | 53 | 30 | 28 | 10 | 9 | 10 | 9 |
| | አማካይ | 59 | 55 | 21 | 19 | 15 | 14 | 12 | 11 |

ጥያቄ 11 የሰዋስው ይዘቶችን አዕምሮዊ ይዘቶችን በማዛመድ ለመማር የሚያስችሉ ብልሃቶችን አዛውትረው በመጠቀም ደረጃ ያላቸውን ልምድ ለማወቅ የቀረበ ሀሳብ ነው። በዚህ መሰረት በፍጹም የማይጠቀሙ መሆኑን ያመለከቱት ተማሪዎች 55 (52%) ሲሆኑ፣ በአብዛኛው የሚጠቀሙት ተጠኚዎች 24 (23%) ያህል ናቸው። ሁል ጊዜ የሚለውን አማራጭ የሰጡት 16 (15%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣አልፎ አልፎ የሚለውን አማራጭ የመለሱት 11 (10%) ያህል ተማሪዎች ናቸው።

እዚህ ላይ የተማሪዎቹ የብልሃት አጠቃቀም መጠን 48% ላይ እንደሚገኝ መረጃው አመልክቷል። ተማሪዎች አዕምሮታዊ ምስልን በመጠቀም ደረጃ ዝቅተኛ አጠቃቀም ያላቸው በመሆናቸው ከነ (O' Malley (1990); Oxford 1990) አስተሳሰብ ጋር የሚዛመዱ ሆኖ አልተገኘም። ለምሳሌ፡- ስዕል፣ ሰንጠረዥ፣ ግራፍ ወዘተ ጋር በማያያዝ አዕምሮዊ አይረሴነት የመፍጠር ብልሃቶችን የመጠቀም እጥረት መኖሩን ያሳያል (O'Malley, 1987; Oxford, 1990)።

ጥያቄ 12 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ለመማርና በሚገባ ለመረዳት ፍሬ ነገሮቹን በማቅለም፣ በማክበብ፣ በማስመር ይጠቀሙ እንደሆነ ለመፈተሽ የቀረበ ሀሳብ ነው:: በዚህ መሰረት ፍጹም የማይጠቀሙበት 64 (60%) ተማሪዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ የሚለውን አማራጭ 20 (19%) ተጠኚዎች መልሰዋል:: ከዚህም ሌላ በኣብዛኛው የሚጠቀሙበት 15 (14%) ተማሪዎች ሲሆኑ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት 7 (7%) ተማሪዎች ሆነው ተገኝተዋል::

እዚህ ለይ የተማሪዎቹ የብልሃት አጠቃቀም በምዕራፍ ሁለት በቀረበው የድርሳሃን ክለሳ ትውረቶች ጋር የሚስማማ ሆኖ አልተገኘም:: ለምሳሌ Oxford (1990) እንደሚገልጹት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ሲማሩ ፍሬ ሀሳቡን ከስር በማስመር፣ በማክበብ፣ በመቀባት ወይም በመለማመጃ ደብተር እና ጥቁር ሰሌዳ ላይ ያረፈበትን ልዩ ቦታ ለማስታወስ ነው (Oxford, 1990):: ነገር ግን ተጠኚ ተማሪዎች የሰጡት መረጃ ከዚይ ሀሳብ የሚለይ ሆኖ ተገኝቷል:: የዚህ ምክንያቱ በተማሪዎች እና በመማር ብልሃቶቻቸው መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል:: ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ማስታወሻ የመያዝ ችግር ሊኖር ይችላል::

ጥያቄ 13 ግራፎችን፣ ሰንጠረዦችን በመጠቀም ሰውስው ይዘቶችን የሚማሩበትን ሁኔታ ለመፈተሽ ከቀረቡላቸው አማራጮች ፍጹም የማይገለገሉበት 60 (57%) ተማሪዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ የሚለውን 21(20%) ተማሪዎች መርጠዋል:: ከዚህ በተጨማሪ በኣብዛኛው የሚለውን የመረጡት 11 (10%) ያህል ተማሪዎች ሲሆኑ 14 (13%) ተጠኚዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው::

ይሁን እንጂ የመማር ብልሃቶችን ባህሪያትና አገልግሎት ተመረማሪዎች በመጠይቁ በቀረቡት ቋንቋን መማር እንደሚቻል የሚገልጹ ቢሆኑም ተማሪዎች እንዳልተጠቀሙባቸው ያመለክታል:: የዚህ ምክንያቱ መምህራን እነዚህን ብልሃቶች በመጠቀም መማር የሚቻል መሆኑን በተግባር በመማርያ ክፍል ውስጥ እንደማይተገብሩት ተማሪዎቹንም እንደማይደግፏቸው ያረጋግጣል::

ጥያቄ 14 የመምህራንና የክፍል ውስጥ ማስተካከያና እሪምትን በመከተል የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ለመማር የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ለማወቅ ሀሳብ ቀርቧል:: ይህንን ብልሃት ፍጹም አንጠቀምበትም ያሉት 56 (53%) ተጠኚዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ተማሪዎች 30 (28%) ናቸው:: በእነዚህ ብልሃቶች በኣብዛኛው የሚማሩ 10 (9%) ተጠኚዎች ሲሆኑ ሁል ጊዜ የሚለውን አማራጭ የመለሱት 10 (9%) ተማሪዎች ናቸው::

የጥናቱ ተሳታፊ አብዛኞቹ ተማሪዎች የመምህራንን ማስተካከያና እርማት የመማር ብልሃት መሆኑን በማወቅ ለመጠቀም እንዳልቻሉ መረጃው ያመለክታል። ሆኖም ብልሃቱ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ታላሚውን የሰዋስው ይዘት በቀጥታ ለመማር የሚያገለግል መሆኑን Oxford (1990) ያስረዳሉ (Oxford, 1990)። ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የሚሰጡ ማስተካከያዎችን በመከታተል የሚጠቀሙባቸው በመምህራን የሚሰጥ ድጋፍ አነስተኛ ነው የሚል ስሜት አድሮባቸው ሊሆን ይችላል ወይም የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን መማር ከባድ አድርገው ሊያስቡም ይችላሉ።

እያንዳንዱን ብልሃት አስመልክቶ ከተጠኚዎች የተገኙት መረጃዎች በአዕምሮታዊ ብልሃቶች ሰንጠረዦች ላይ  መመልከት እንደሚቻለው፣ በአማካይ ከተወሰደው መረጃ 51(48%)የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች አእምሮታዊ ብልሃቶችን በተለያየ የአጠቃቀም ደረጃ የሚገለገሉባቸው ሆነው ተገኝተዋል። በተለይም ከአእምሮታዊ ብልሃቶች መካከል ሰዋስዋዊ መልመጃዎችን መስራትና ልምምዶችን ማድረግ የመማር ብልሃቶች ናቸው። በመጠይቅ 9 እና 10 ላይ በግልጽ እንደሚስተዋለው ሰዋስዋዊ ልምምድን ማጠናከር እና መልመጃዎችን በቤትና በክፍል ውስጥ መስራት የተማሪዎቹ ተዘውታሪ ብልሃቶች መሆናቸውን ከጥናቱ የተገኘው መረጃ አረጋግጧል። ስለሆናም ተማሪዎች ስለ አእምሮታዊ ብልሃቶች ያላቸውን አጠቃላይ ዕውቀት ለመመርመር ከቀረቡላቸው መጠይቆች መካከል አብዛኛው የሚጠቀሙባቸው ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግን እና መልመጃዎችን መስራት ሙሉ አዕምሯዊ እውቅና ሰጥተዋቸዋል። ተጠኚ ተማሪዎች የሰጡት መረጃም የሚያረጋግጠው የተጠቀሱት ሁለቱ ተመራጭ መሆናቸውን ነው።

በአጠቃላይ አንድ፣ ሁለትና ሦስት አዕምሮታዊ ብልሃቶች ከአንድ እስከ አሥራ አራት ለተጠኚ ተማሪዎች በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ይሁን በቃለመጠይቅ በአዕምሮታዊ ብልሃቶች በተገኘው መረጃ መሠረት ሰዋሰውን ለመማር በፍጹም የማይቅሙ መሆኑን የመለሱ ተማሪዎች በአማካይ 55 (52%) መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ በብቃት የተጠቀሙ አለመሆኑን በመተንተን የጥናቱ ውጤት ያሳያል። በአንጻሩም ሰዋስዋዊ ልምምድ ማጠናከር እና መልመጃዎችን በመሥረት መማር ከተሳታፊ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ የመረጃው ትንተና ውጤት አሳይቷል።

### 4.1.2. ማህደር-ትውስታ ጥቅል መረጃ ትንተናና ውጤት

ከ 15_23 በጽሑፍ መጠይቁ ውስጥ የተጠቀሱት ሀሳቦች በድርሳን ክለሳው በሰፊው የተብራሩትን የማህደር_ትውስታ ብልሃቶች የያዙ ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች በተማሪዎች

አንጻር ያላቸውን የተውዛታሪነት ደረጃ ለማወቅ የተደራጁ መጠይቆች በሰንጠረዥ 4 ቀርበው ተተንትነዋል።

ከዚህ በማስከተል በሰንጠረዥ ለተማሪዎች የቀረቡትን ዝርዝር ትውስታ ብልሃቶች የሚመለከት ትንተና በማቅረብ በድርሳን ክለሳው ካሉት ትውረቶች ጋር Oxford (1990: 138) እና O'Malley (1990) ለትውስታ ብልሃቶች ከቀረቧቸው ፍሬ ነገሮች ጋር በመመሳከር መረጃውን ለማሳየት ይሞክራል (O'Malley, 1987; Oxford, 1990)።

*ሠንጠረዥ 4 የማህደር_ትውስታ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ*

| ተ.ቁ | ብልሃቶች | የአጠቃቀም ተዘውታሪነት አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፍጹም | | አልፎአልፎ | | በአብዛኛው | | ሁልጊዜ | |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| 15 | በቃል ለመያዝ ሽምደዳ በመጠቀም መማር | 36 | 34 | 15 | 14 | 35 | 32 | 20 | 19 |
| 16 | ሀረጋትን አወቃቀር መተንተን | 64 | 60 | 23 | 22 | 10 | 9 | 9 | 8 |
| 17 | በመናገር ጊዜ ሰዋስውን ማስታወስ | 63 | 59 | 17 | 16 | 15 | 14 | 11 | 10 |
| 18 | ድምጽን፣ የቃልና የሀረግ መከለስ | 57 | 54 | 26 | 25 | 15 | 14 | 8 | 8 |
| 19 | የሰዋስው መጽሓፍትን ማንበብ | 65 | 51 | 27 | 25 | 0 | 0 | 14 | 14 |
| 20 | ለማስታወስ ልዩ ምልክት መጠቀም | 20 | 19 | 18 | 17 | 57 | 54 | 11 | 10 |
| 21 | እንደገና በመተንተን ማስታወስ | 58 | 55 | 19 | 18 | 17 | 16 | 12 | 11 |
| 22 | የቃላትን አደራደርህ ግን መገንዘብ | 46 | 43 | 42 | 40 | 8 | 8 | 10 | 9 |
| 23 | ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ሲማሩ ማስታወሻ መጻፍ | 36 | 34 | 41 | 39 | 18 | 17 | 11 | 10 |
| | አማካይ | 49 | 47 | 25 | 24 | 19 | 18 | 12 | 11 |

ጥያቄ 15 የሰዋስው ፍሬ ነገሮችን ለተግባቦት ለመጠቀም እንዲያመቻቸው በቃላቸው ሸምድደው በመያዝ የመማር ልምድ እንዳላቸው ለማረጋገጥ መጠይቁ ቀርቧል፡፡በተገኘው ውጤት መሰረትም ይህንን የመማር ብልሃት ፍጹም የማይጠቀሙበት 36 (30%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ በአብዛኛው ያሉ 35 (32%)ተጠኚዎች ናቸው፡፡ በአንጻሩ ሁል ጊዜ የሚለውን አማራጭ የመለሱት 20 (19%)ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ የሚየጠቀሙበት 15(14%) ተጠኚዎች ናቸው፡፡ የቀረበው መረጃ የሚያመላክተው የተማሪዎች ብልሃት አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆኑንነው፡፡

በአንጻሩ በምዕራፍ ሁለት Ellis (1989; 76-7) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ትምህርት በተቀላጠፈ መንገድ ለመማር በቃል መሸምደድ አንዱ ብልሃት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ይህን ብልሀት ተማሪዎቹ በስፋት አለመጠቀማቸው ምናልባትም ይህን ብልሃት ለመጠቀም በጓደኞቻቸውና በመምህራን የሚያበረታታ ሁኔታ ሳያገኙ ቀርተው ሊሆን ይችላል፡፡

ጥያቄ 16 የቃላትና ሀረጋትን አወቃቀር በመለየት ሰዋስዋዊ አደራደሩን በመተንተን መማርና በትውስታ ውስጥ ማስገባት ለመገልገል መቻል ያለውን ተውዛታሪነት ለመፈተሽ የቀረበ ሀሳብ ነው፡፡ ይህንን የትውስታ ስልትበፍጹም አንጠቀምም ያሉት 64 (69%) ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት 23 (22%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ በአብዛኛው የሚጠሙበት 10 (9%) ተጠኚዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ሲሉ የመለሱ 9 (8%) ተማሪዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ይህ መረጃ የሚያስገነዝበው የተማሪዎች አጠቃቀም ሁኔታ ከመምህራን አስተሳሰብ አንጻር የተስማማ አለመሆኑን ነው፡፡ Oxford (1990) አዳዲስ የሰዋስው መዋቅሮችን ለመማር ቃላትን በየወገናቸው በማቧደን ለማስታወስ መሞከር፣ ትርጉም ሰጪ አሃዶችን፣ ፍቺዎቻቸውን፣ ጊዜያተ_ሰዋስውን (ሩቅ አላፊ፣ቅርብ አላፊ፣ የትንቢት ጊዜ ወዘተ) በልዩ ልዩ ምልክቶች በመጠቀም ለመያዝ መሞከር ምርጥ የመማር ብልሃት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በአንጻሩ በዚህ ጥናት የተገኘው መረጃው ከዚህ የተፋለሳ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ጥያቄ 17 የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የተማሯቸውን የሰዋስው ይዘቶች በሚያነቡበትና በሚያደምጡበት ጊዜ ልብ ብለው በማስታወስ ትምህርቱን ለመገንዘብ ጥረት ያደርጉ እንደሆነ ለመፈተሽ የቀረበ መጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ብልሃት ፍጹም የማይጠቀሙበት 63 (59%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ የሚገለገሉበት 17 (16%) ተማሪዎች ናቸው፡፡

በአብዛኛው ያሉ 15 (14%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን በማለት ምላሻቸውን የሰጡት ደግሞ 11 (10%) ተማሪዎች ናቸው::

ከዚህ ጋር በተገናኘ Stern(1983) እንዳስረዱት፣ በማዳመጥና በማንበብ ጊዜ ተማሪዎች የተማሯቸውን የሰዋስው ቁምነገሮች ከራሳቸው ጋር በማዋሀድ የሚጠቀሙበት ብልሃት መሆኑን ቢጠቁሙም በዚህ ጥናት ግኝት መሰረት ግንየተማሪዎቹ አጠቃቀም አነስተኛ ሆኖመገኘቱን መረጃው አሳይቷል ::

ጥያቄ 18 የአማርኛን ቋንቋን ድምጾች፣ ምዕላዶችን፣ የቃላትን ባህሪያትና ዝምድና በሚገባ በመተንተን እያንዳንዱን አሃድ ለማስታወስ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚመለከት ብልሃት ፍጹም አንጠቀምበትም ያሉ 57 (54%) ተጠኚዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ በማለት የመለሱት 26 (25%) ተማሪዎች ናቸው:: በአንጻሩ በአብዛኛው የሚለውን አማራጭ የመለሱ 15 (14%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ሁልጊዜ የሚለውን አማራጭ የመለሱ 8 (8%) ተማሪዎች ሆነው ተገኝተዋል::

ሰዋስውን ለመማር ወሳኝ የሚባለውን መጠይቅ በአጠቃቀም ደረጃ ተማሪዎች ትክክለኛውን ሀሳብ አቅርቧል ማለት አያስችልም:: ይህ የሚያመለክተው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚማሩትን ሰዋስዋዊ ይዘት በትንተና ስልት መማራቸውን የማያስታወሱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው::

ጥያቄ 19 በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሯቸውን የሰዋስዋዊ ይዘቶች የበለጠ አጠናክረው በረጅም ጊዜ የትውስታ ብልሃት ውስጥ በማከማቸት በአስፈላጊው ጊዜ እንደገና በማውጣት ለመጠቀም እንዲችሉ የሰዋስው መጽሃፍትን በማንበብ እውቀታቸውን ስለማደበራቸው የሚመለከት ሀሳብ የቀረበበት ሆኖ፣ ፍጹም አንጠቀምበትም ያሉት 65 (61%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ ያሉት 27(25%) ተጠኚዎች ናቸው:: በአንጻሩ በአብዛኛው የሚለውን የመረጡ የሌሉ ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ ያሉት 14(13%) ተማሪዎች ናቸው::

ይህን ብልሃት በሚመለከት ያላቸው የአጠቃቀም ሁኔታ አነስተኛ መሆኑን መረጃው ጥቆማ የሚሰጥ ነው::

ጥያቄ 20 የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የተማሩትን የሰዋስው ይዘት በቀላሉ ለማስታወስ ይችሉ ዘንድ የሰዋስው ትምህርቱን የተማሩበትን ደብተር፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ማስታወሻ ወረቀት፣ ወዘተ. በማስመር፣ በማክበብ፣ወይም ልዩ ምልክት በመጠቀም የሚማሩ መሆናቸውም ለማረጋገጥ

የቀረበ ሀሳብ ነው፣ በዚህ ብልሃት በአብዛኛው እንደምገለገሉበት መረጃ የሰጡት 57 (54%) ሲሆኑ፣ በፍጹም አንጠቀምበትም ያሉ 20 (19%) ተማሪዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ አልፎ አልፎ እንደምጠቀሙበት የገለጹት ተጠኚዎች18 (17%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ይህንን ብልሃት ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት መሆናቸውን ያመለከቱት 11 (10%) ተማሪዎች ናቸው።

ይህ ብልሃት በክለሳ ድርሳኑ ከቀረበው ከOxford (1990)እና O'Malley (1990) ካነሱት ሀሳብ ጋር የተጣጣመ ሲሆን፣ ከቀደምት ጥናቶች ከተደረሰባቸው ውጤቶች ይርጋ (1997) "ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች" ይገለጉሉባቸዋል ከተባሉት የመማር ብልሃቶች ጋር ስምሙ ነው (O'Malley, 1987; Oxford, 1990; ይርጋ, 1997)።

ጥያቄ 21 ተማሪዎች አዲስ የተማሩትን የሰዋስው መዋቅር መልሶ በማስታወስ ይማሩ እንደሆነ ለመመርመር የቀረበ ሀሳብ ነው። ይህንን ብልሃት ፍጹም አንጠቀምበትም ያሉ 58 (55%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙበት 19 (18%) ተማሪዎች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ በአብዛኛው ያሉት 17 (16%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን በማለት የመለሱት 12 (11%) ሲሆን በየአጠቃቀም ደረጃቸው የተለያየ ቢሆንም 48 (45%) ተጠቃምተማሪዎች ናቸው።

እነዚህ ብልሃት ላይ ተማሪዎች አጠቃቀማቸው አነስተኛ በመሆኑ በብልሃቱ እንዲጠቀሙ የመምህራን ግፊት እንደሚያስፈልግ ፊንጭ የሚሰጥ ነው።

ጥያቄ 22 የቀደመ የሰዋሰው እውቀታቸውን አዲስ ከሚማሩት ሰዋስዋዊ ትምህርት ይዘት ጋር በማዛመድ ሰፊ ሀሳብን ለመግለጽ የሚያስችሉ ሀረጋትና አረፍተ ነገሮችን በመስራት የትውስታ ብልሃትን የአጠቃቀም ልምዳቸውን ለፈተሽ የቀረበ መጠይቅ ነው። የቀረበውን ብልሃት ፍጹም የማይጠቀሙበት 46 (43%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ ያሉት 42 (40%) ተማሪዎች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የዚህን ብልሃት ተዘውታሪነትን አስመልክተው በአብዛኛው ያሉት 8 (8%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ ያሉት 10 (9%) ተጠኚዎች ናቸው።

እውቀት ተደጋጋፊ መሆን ይኖርበታል፤ የአሁኑ የቀደመውን የሚያበለጽግ እንዲሆን ያስፈልጋል። Oxford (1990;41) ያለፈውን ሰዋስው ይዘት ካሁኑ ጋር ሲያዛምዱ ተማሪዎች ውጤታማ ሊሆኑ እንደምችሉ ይገልጻል። ነገር ግን ይህን ብልሃት ተማሪዎች ሲጠቀሙበት አልታየም (Oxford, 1990)።

ጥያቄ 23 ተጠኚ ተማሪዎች የተማሩትን ለማስታወስ ያመቻቸው ዘንድ እነሱን በሚገባቸው መንገድ የሰዋስው ይዘቶችን ሲማሩ አጫጭር ማስታወሻዎችን በመመዝገብ የሚማሩ ስለመሆናቸው ያላቸውን ልምድ ለመመርመር የቀረበ መጠይቅ ነው። አልፎ አልፎ እንጠቀማለን በማለት የመለሱት 41 (39%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ይህን ብልሃት በመጠቀም ተማሪዎች የሚኖራቸውን ልምድ ለቀረባቸው አማራጭ ፍጹም አንጠቀምበትም ሲሉ የመለሱት 36 (34%) ተጠኚዎች ናቸው።በሌላ በኩል በአብዛኛው ያሉ18(17%) መላሾች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 11(10%) ተማሪዎች ናቸው።ከትውስታ ብልሃቶች መካከል በተማሪዎች ተዘወትረው ለሰዋስው ትምህርት መማርያ የሚጠቀሙባቸው መኖራቸውን መረጃው ጠቁሟል።

የመጀመሪያው ልዩ ልዩ ምልክቶችን (ፍሬ ሀሳቡን ከስር በማስመር፣ በማክበብ፣ በመቀባት ወይም በመለማመጃ ደብተርና ጥቁር ሰሌዳ ላይ ያረፉበትን ልዩ ቦታ ለማስታወስ በመሞከር) በመጠቀም በተራ ቁጥር 20 እንደተመለከተው 57 (54%) ተማሪዎች በኣብዛኛው የሰዋስው ይዘቶችን የሚማሩባቸው ዋና መንገዶች ናቸው። በሁለተኛ ደረጃ በተራ ቁጥር 23 የተመለከተው ማስታወሻ መጻፍ 41 (39%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ የሚማሩበት ብልሃት ሆኖ ተገኝቷል። አጠቃላይ የሰንጠረዡን መረጃ ውጤት ስንመለከተው በአማካይ 49 (47%) የሚሆኑ ተማሪዎች የትውስታ ብልሃትን የማይጠቀሙ ሆነው ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ በጽሑፍ መጠይቆችም ሆነ በቃል መጠይቆች መሰሪያነት በተገኘው መረጃ መሰረት የትውስታ ብልሃቶችን በመጠቀም ለመማር ያላቸውን የተዛውታሪነት ሁኔታ ለመተንተን ተሞክሯል። ከትንተናው በተገኘው መረጃ መሰረት የትውስታ ብልሃቶች የሰዋሰውን ለመማር አልፎ አልፎ፣ በአብዛኛውና ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ የገለጹት ተጠኚዎች ዝቅተኛውን ቁጥር የያዙ በመሆናቸው (የአጠቃቀም ደረጃ ልዩነት ቢኖርም) የሚዛወተሩ አይደሉም ማለት ይቻላል።

በክፍል ውስጥ የሚቀርብላቸውን ሰዋሰዋዊ ትምህርት የሚማሩባቸው ሌሎች ብልሃቶች እንዳላቸው ለተጠየቁት ክፍት መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የለም። ነገር ግን እነዚህ ብልሃቶች አንዳንድ ቃላትን፣ ጥያቄዎችና ድምጾችን ለማስታወስ እንደሚጠቅሟቸው 5 ተማሪዎች ምላሻቸውን ሰጥተዋል። ይህን የትውስታ ብልሃቶችን ጠቀሜታ ለማሳየት ፍንጭ የሚሰጥ ነው።

### 4.1.3. የአካካሽ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ ትንተናና ውጤት

በአካካሽ ብልሃቶች አኳያ ተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ አራት መሰረታዊ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በሰንጠረዥ አምስት እንደሚታየው ከተራ ቁጥር 24_27 ድረስ ያሉት ናቸው።

በተተኳሪው ቋንቋ ለመገልገል ተማሪው የሚገጥመውን ችግር የማወቅ ብቻ ሳይሆን በጠፋው መዋቅር ምትክ የአፍልቆት ብቃቱን በመጠቀም ችግሩን የሚያቃልልባቸው ብልሃቶች ናቸው Oxford (1990)። ለተማሪዎች በመጠይቅ የቀረቡት ብልሃቶች ዝርዝር ትንተናና በምዕራፍ ሁለት ከቀረበው የቋንቋ መማር ብልሃቶች ትውረት ጋር በማነጻጸር ለማቅረብ ተሞክሯል (Oxford, 1990)።

*ሠንጠረዥ 5 የአካካሽ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ*

| ተ.ቁ | ብልሃቶች | የአጠቃቀም ተዘውታሪነት አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፍጹም | | አልፎአልፎ | | በአብዛኛው | | ሁልጊዜ | |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| 24 | በመናገርና በመጻፍ ጊዜ ችግሮችን ለማቃለል ልዩ ልዩ መዋቅሮችን መጠቀም | 31 | 29 | 15 | 14 | 35 | 33 | 25 | 24 |
| 25 | የሚከብዱ መዋቅሮችን በጅምር በመተው ማስተካከያ መጠየቅ | 55 | 52 | 19 | 18 | 16 | 15 | 16 | 15 |
| 26 | የሚከብዱ መዋቅሮችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመጻፍ መጥራት | 50 | 47 | 33 | 31 | 10 | 9 | 13 | 12 |
| 27 | በንግግርና በንባብ ጊዜ የሚያስቸግሩ ድምጾችን በዝምታ መተው | 16 | 15 | 27 | 25 | 59 | 56 | 4 | 4 |
| | አማካይ | 38 | 36 | 24 | 23 | 30 | 28 | 15 | 14 |

ጥያቄ 24 ተማሪዎች በመናገርና በመጻፍ ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማቃለል ልዩ ልዩ መዋቅሮችን በመጠቀም ለምሳሌ፡- የቃላትን ተተኪ ፍቺ፣ በመጥበቅና መላላትን፣ የእምርነትና የተባዕት ጾታ አመልካችን፣ የቃላትን ምስረተ ቅጥያዎችን ወዘተ እያቀያየሩ የአካካሽ ብልሃት ስለመገልገላቸው የቀረበ መጠይቅ ነው። በዚህ ብልሃት በአብዛኛው እንጠቀምበታል ያሉት 35 (33%) ሲሆኑ፣ ፍጹም አንጠቀምበትም ያሉት 31 (29%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ

እንጠቀምበታለን ያሉት 15 (14%) ተጠኚዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች ፣ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 25 (24%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ተማሪዎች የተጠቀሰውን የመማር ብልሃት በአብዛኛው እንደምጠቀሙበት መረጃው ያመለክታል፡፡ ከይርጋ(1997) የጥናት ውጤትን ጋር ስምሙ ሆኖ ተገኝቷል (ይርጋ, 1997)፡፡

ጥያቄ 25 የጥናቱ ተተኳር ተማሪዎች የሚከብዷቸውን ድምጻ ልሳናት፣ምዕላዶችና ሀረጋትን በጅምር በመተው ሌሎች አካላት ለምሳሌ፡- መምህራን፣ ጓደኛ፣ ቤተሰብ ወዘተ ማስተካካያ እንዲያደርጉላቸው በመጠየቅ ይማሩ እንደሆነ ሀሳብ ቀርቦላቸዋል፡፡ በዚህ ብልሃት ፍጹም አንጠቀምበትም ያሉት 55(52%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት 19(18%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአብዛኛው የሚጠቀሙበት መሆኑን 16 (15%) ተማሪዎች የገለጹ ሲሆን፣ሁል ጊዜ በማለት የመለሱ 16(15%) ተማሪዎች ናቸው፡፡

በመሆኑም Stern (1983;411-12) እንደሚያስረዱት የሁለተኛ ቋንቋ ጥሩ ተማሪዎች የቋንቋውን ውስጣዊ መዋቅር በተገቢ መንገድ አስተካክለው መጠቀም እስኪችሉ ድረስ ጥረታቸውን የሚያቋርጡ በመሆናቸው የቋንቋ ስርኣትን የመማርብልሃትን ከመገልገል ወደ ኋላ አይሉም" ሲሉ ከገለጹት ጋር የሚቃረን ነው፡፡

ጥያቄ 26 በከምባትኛ ቋንቋ አፊቸውን የፈቱ የ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን የሚማሩበት ጊዜ የሚከብዱ ድምጾችን፣ ምዕላዶችን፣ አረፍተ ነገሮችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመጻፍ የሚያስቸግረውን የሰዋስዋዊ ይዘት ለመማር ያላቸውን የመማር ልምድ ለመመርመር የቀረበ የአካካሽ ብልሃት ነው፡፡ በመሆኑም ብልሃቱን ተዘውታሪነት በሚመለከት ከቀረቡላቸው አማራጮች መካከል ፍጹም አንጠቀምበትም በማለት ሀሳባቸውን የገለጹት 50 (47%) ተማሪዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡ 33 (31%) ያህል ተጠኚዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁል ጊዜ በዚህ ብልሃት እንደምገለገሉ ምርጫቸውን የሰጡት 13 (12%) የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ሲሆኑ፣ በአብዛኛው በማለት 10 (9%) ያህሉ የጥናቱ ተተኳሪዎች ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ብልሃት ተማሪዎች ትምህርት በሚከታተሉበት ጊዜ ተማሪዎች የሚጠፏቸውን የቋንቋ መዋቅሮች ወድያው በመተካት በመማር የሚያስችላቸው መሆኑን ምሁራን ቢያስረዱም (Stern 1983) የተማሪዎች አጠቃቀም ግን አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል (Stern, 1983)፡፡

ጥያቄ 27 በንግግርና በንባብ ጊዜ የሚያስቸግሩ ድምጾችን ወይም ጥያቄዎችን በዝምታ ወይም በማቅማማት ድጋፍ የሚያስጠይቅ የአካካሽ ብልሃትን በመገልገል የመማር ልምዳቸውን ለመፈተሽ የቀረበ መጠይቅ ነው። ብዙዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በንግግር ወይም በጽህፈት ወቅት የታላሚውን ቋንቋ ድምጾች ለመጥራት ብቸገሩም ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ራሳቸውን አደፋፍረው ቋንቋውን የሚማሩ መሆናቸውን Oxford (1990) ይገልጻሉ (Oxford, 1990)። በመሆኑም ይህንን ብልሃት በአብዛኛው የሚጠቀሙበት 59(56%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙበት 27 (25%) ተማሪዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ፍጹም የማይጠቀሙበት 16 (15%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ሁልጊዜ የሚጠቀሙበት 4 (4%) ተማሪዎች ናቸው።

የአማርኛ ሰዋስውን በሚማሩበት ጊዜ በዝግ መጠይቁ ከቀረቡት ውጭ ሌሎች ብልሃቶችን ይጠቀሙ እንደሆነ ለቀረበላቸው መጠይቅ የጻፉት ምላሽ የለም። ነገር ግን የሚጠፉባቸው የቋንቋ አጠቃቀሞች አፍ በፈቱበት ቋንቋ የሚተኩ መሆናችውን 3 ተማሪዎች ጠቁመዋል። በአጠቃላይ አካካሽ ብልሃቶች ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር የሚጠበቀውን ያህል በተማሪዎች እውቅና ያላቸው ሆነው አልተገኙም።

የእያንዳንዱ ጥያቄ ትንተና በዝርዝር የቀረበ ቢሆንም ከቀረበው ሰንጠረዥ የአካካሽ ብልሃቶችን አጠቃላይ ውጤት ግን በአጭሩ መናገር ይቻላል። ይህም ከተጠኚ ተማሪዎች 35 (33%) ያህሉ የሰዋስው ትምህርትን ለመማር የሚጠቀሙባቸው የማተካካት ብልሃት የሚባሉት ሲሆኑ፣ ትምህርቱ ሂደት ከባድና የሚያስቸግሩ የሰዋሰው ይዘቶችን በዝምታ መተውና በሌሎች ድጋፍ እንዲሟሉ ማድረግ በ 59(56%) ተማሪዎች ተመራጭ የሆኑ ብልሃቶች ሆነው ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ አካካሽ ብልሃቶች ለአማርኛ ሰዋሰው ትምህርት መማሪያነት በአማካይ 38 (36%) ተማሪዎች የማይጠቀሙባቸው መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል። ከነዚህ ብልሃቶች የቋንቋን መዋቅር የሚማር ተማሪ የመረጃ ክፍተት ሲያጋጥመው በቀልጣፋ ሁኔታ የሚያሟለበቸው ብልሃቶች ናቸው።

ይህ የአካካሽ ብልሃቶች ከተራ ቁጥር 24-27 ከተጠኚ ተማሪዎች ከቀረበው በጽሑፍ መጠይቆች ሆነ በቃል መጠይቆች በተመለሰው መረጃ ተማሪዎች ሰዋሰውን ሲማሩ የሚከብዱ መዋቅሮችን በጅምር በመተው ማስተካካያ መጠይቅ በጭራሽ በማለት ምላሽ የሰውጡት 55 (52%) የሚከብዱ መዋቅሮችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በመጻፍ መጥረት በፍጹም ያሉት 50 (47%) አልፎ

አልፎ ያሉት ደግሞ 33 (31%) ተጠኚ ተማሪዎች ሲሆኑ በፍጹምና አልፎ አልፎ በማለት በተገቢ የማይጠቀሙ መሆኑን የትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡

## 4.2 ኢ-ርቱዕ የመማር ብልሃቶች

ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ውጤታማ እንዲሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሊፈጽሟቸው የሚገቡ የቋንቋ መማር ተግባራትን የሚያመቻቹ ተግባራት ናቸው፡፡ እነዚህ ብልሃቶችበሁለተኛው ቋንቋ ትምህርት ሂደት ወቅት ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት ያላቸው ሳይሆኑ ርቱዕ የመማር ብልሃቶችን ደጋፊዎች ናቸው፡፡ ኢ-ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ልዕለ አእምሮታዊ (ግለ-አዕምሮታዊ)፣ ስሜት ነኪ ቁጥጥርና ማህበራዊ ተብለውበ 3 ንዑሳን ብልሃቶች እንደሚከፈሉ ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ተብራርተዋል፡፡ በመሆኑም በነዚህ ንዑሳን ብልሃቶች ውስጥ የሚካተቱትን የቋንቋ መማር ብልሃቶች በመጠይቅ ቀርበው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው መማሪያነት የሚዘወተሩት የትኞቹ እንደሆኑ ለመተተንና ለመለየት ጥረት ተደርጓል፡፡

### 4.2.1 ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃትንተናና ውጤት

ከተራ ቁጥር 28_33 የቀረቡት የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን የሚመለከቱ የቀረቡ መጠይቆች ናቸው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው የሚማረውን ትምህርት ቅድመ ዝግጅት አድርጎበት፣ እቅድ አውጥቷል፣ የሚማረውን የትምህርት ይዘት በተግባር መከናወኑን የሚገመግሙባቸው እነዚህ ብልሃቶች ለተማሪዎች በመጠይቅ ቀርበው በተሰበሰበው መረጃ መሰረት (እያንዳንዱ መጠይቅ ላይ ዝርዝር ትንተና የሚቀርብበት ቢሆንም) የሚከተለው አጠቃላይ ውጤት ተገኝቷል፡፡

ይህ ለምን ሊሆን ቻለ? የሚለው ጥያቄ በሚቀጥሉት የእያንዳንዱ መጠይቅ የውይይት ክፍል የሚቀርብ ይሆናል፡፡

*ሠንጠረዥ 6የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ጥልቅ መረጃ*

| ተ.ቁ | ብልሓቶች | የአጠቃቀም ተዘውታሪነት አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፍጹም | | አልፎአልፎ | | በአብዛኛው | | ሁልጊዜ | |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| 28 | ለመማር ዝግጅት ማድረግ | 61 | 58 | 23 | 22 | 17 | 16 | 5 | 5 |
| 29 | ሰዋስውን ለመማር ቀድመው ማደረጃት | 59 | 56 | 28 | 26 | 12 | 11 | 7 | 7 |
| 30 | ሰዋስውን ለመረዳትና ለመገንዘብ እቅድ ማጣት | 57 | 54 | 25 | 24 | 18 | 17 | 6 | 6 |
| 31 | የተሰሩ የሰዋስው የስህተት ምንጮች መገምገም | 20 | 19 | 59 | 56 | 8 | 8 | 19 | 18 |
| 32 | ለሰዋስው ትኩረት በመስጠት ግላዊ ድጋፍ ማመቻቸት | 59 | 56 | 14 | 13 | 24 | 23 | 9 | 8 |
| 33 | የስህተት ምንጮችን በመለየት ግላዊ ግምገማ ማድረግ | 21 | 20 | 53 | 50 | 22 | 21 | 10 | 9 |
| | አማካይ | 46 | 43 | 34 | 32 | 17 | 16 | 9 | 8 |

ጥያቄ 28 የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃት አካል የሆነውን ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ለመማር አዕምሮዊ ቅድመ ዝግጅትና አላማ የመሰነቅን ብልሃት በመጠቀም ስለመማር አለመማራቸው ለማወቅ የቀረበ መጠይቅ ነው:: በዚህ መሰረት ይህንን ብልሃት ፍጹም የማይጠቀሙበት 61 (58%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙበት 23 (22%) ያህል የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ናቸው:: በአብዛኛው ያሉት 17 (16%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ እንማራለን ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 5 (5%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው::

ከጥናቱ ከተገኘው መረጃ ይህ ብልሃት በተማሪዎች የሚዘወተር ካለመሆኑም በላይ ብዙም እውቅና ያለገኙ መሆኑ ተረጋግጧል:: ይሁን እንጂ Brown (2002;XII) Oxford (1990) እንደሚያስረዱት ቋንቋን ለመማር ግብ መጣል፣ ሰፊና ጥልቅ ልምምድ ማድረግ፣ስህተቶችን መተንተን፣ ከስህተቶች መማር ወሳኝ ብልሃቶች ናቸው:: ስለሆነም ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች በሰዋስው ትምህርት ወቅት አለመጠቀማቸው፣ መምህራን የሰዋስውን ትምህርት

በክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ብልሃቶች አጠቃቀምና አተገባበርን በአግባቡ ለይተው እንደማይተገብሩት፣ ተማሪዎቹም በበቂ ልምምድ ስለማይደግፏቸው ነው፡፡ ከሚለው ሀሳብ ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል (Brown, 2002)፡፡

ጥያቄ 29 የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ይዘቶችን ከክፍል ጊዜ በፊት ቀድሞ በማዘጋጀትና በማደራጀት አጠናቀው ወደ ክፍል በመግባት ትምህርታቸውን ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ልምድ ስለመኖር ወይም አለመኖራቸው ለመመርመር የቀረበ ሀሳብ ነው፡፡ ይህንን ብልሃት ፍጹም የማይጠቀሙበት 59 (56%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ እንደሚገለገሉበት ያመለከቱት 28 (26%) ተጠኚዎች ናቸው፡፡ በአብዛኛው እንጠቀምበታለን ያሉ 12 (11%) ሲሆኑ፣ ሁልጊዜ እንደሚገለገሉበት የገለጹት 7 (7%) ይህል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ጽሑፍ መጠይቅ መረጃ አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ 12 ተጠኚ ተማሪዎች ተመሳሳይ ቃለ መጠይ ተጠይቀዋል፡፡ በቃለ መጠይ ውጤት መሰረትም 8 ተማሪዎች ይህን ብልሃት እንደማያዘውትሩ ተረጋግጠዋል፡፡

የተጠኚ ተማሪዎች የአጠቃቀም ልምድ ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ለመማር ቅድመ ዝግጅት የማያደርግ ተማሪ ትምህርቱን በአግባቡ ለመከታተል ችግር ይገጥሟል፡፡ ጠንካራ የቋንቋ ተማሪዎችና ደካማ የቋንቋ ተማሪዎች የሚለያዩት ለትምህርታቸው በሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት መሆኑን Ellis (1989;77) ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ለነዚህ ብልሃቶችን ሆነው እንዲገኙ የሚያበረታታቸው አካል አስፈላጊ መሆኑን መረጃው ፍንጭ ሰጥቷል፡፡

ጥያቄ 30 በከምባትኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች የሚከብዱ የሰዋስው ይዘቶችን በግል ጥረት ለመረዳትና ለመገንዘብ የሚያስችል እቅድ በማውጣት የመማር ልምዳቸውን ለመፈተሽ የቀረበ መጠይቅ ነው፡፡ ይህም ብልሃት ፍጹም የማይጠቀሙበት 57 (54%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣አልፎ አልፎ ይህን ብልሃት የሚጠቀሙበት 25 (24%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ በአብዛኛው የሚጠቀሙበት 18 (17%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ የመማሪያ ብልሃታቸው መሆኑን የገለጹት 6 (6%) ተማሪዎች ናቸው፡፡

ጠንካራ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚማሩትን የቋንቋ ትምህርት በተደራጀ እቅድ የሚማሩ መሆናቸውን በምዕራፍ ሁለት የተጠቀሱት stern (1983;411-12) ያስረዳሉ፡፡ ይህ በተማሪዎች የቀረበ መረጃ ግን በድርሳን ክለሳው ከቀረቡት ሀሳቦች ጋር ያልተስማማ ነው፡፡በመሆኑም የተማሪዎች አጠቃቀም ክፍተት ያለበት መሆኑም ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 31 በመምህር የተሰጡ የቤትና የክፍል የሰዋስው መልመጃዎች በመምህራን ስታረሙ የስህተት ምንጮችን በመገምገም ለሚቀጥለው የትምህርት ሂደት ሁኔታዎችን ስለማመቻቸት ያለውን ግንዛቤ ለማወቅ የቀረበ ነው። ይህንን ብልሃት አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት 59 (56%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ፍጹም አንጠቀምበትም በማለት ሀሳባቸውን የገለጹት 20 (19%) ተጠኚዎች ናቸው። ሁል ጊዜ እንደ ሚገለገሉበት መረጃ የሰጡት 19 (18%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ፣ በአብዛኛው በማለት የመለሱ 8(8%) ተማሪዎች ናቸው።በመሆኑም ይህ ብልሃት በድርሳን ክለሳው ከተገለጹት ትውረቶች ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል።

ጥያቄ 32 በሰዋስው ትምህርት ልዩ ትኩረት በመስጠት ግላዊ ድጋፍ የሚገኝበትን ስልት በማመቻቸት በኩል ያላቸውን አጠቃቀም ልምድ ለመለየት የቀረበ ነው። ይህንን ብልሃት ፍጹም አንጠቀምበትም ያሉት 59 (56%) ሲሆኑ፣በአብዛኛው የሚጠቀሙ መሆናችውን የገለጹት 24 (23%) ተማሪዎች ናቸው። አልፎ አልፎ እንገለገልበታለን ሲሉ መረጃ የሰጡት 14 (13%) ተጠኚዎች ሲሆኑ፣ ከዚህ በተጨማሪ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት 9 (8%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነው ተገኝተዋል።

ስለዚህ ከልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች መካከል አንዱ ለትምህርት ለቀረበው ቋንቋ ትኩረት መስጠት ነው (Oxford,1990;137)። ሆኖም የተገኘው የጥናቱ ውጤት ይህንን የሚደግፍ ሆኖ አልተገኘም (Oxford, 1990)።

ጥያቄ 33 በሰዋስው ትምህርት ሂደት የስህተት ምንጮችን በመለለየት ግላዊ ግምገማ በማድረግ የሚማሩበትን መንገድ ለማወቅ የቀረበ መጠይቅ ነው።ይህንን ብልሃት አልፎ አልፎ እንጠቀሚበታለን ያሉት 53 (50%) ተጠኚዎች ሲሆኑ፣ በአብዛኛው የሚጠቀሙበት 22 (21%) ያህል የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው። ፍጹም አንጠቀምበትም ሲሉ መረጃ የሰጡት 21(20%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ እንጠቀማለን በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 10(9%) ተማሪዎች ናቸው።

በመሆኑም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋው የቃላት፣ የሰዋስው፣ የተናጋሪዎች ባህል እንግዳነት የተነሳ ብዙ ስህተቶችን ልሰሩ እንደሚችሉ ምሁራን ያስረዱና ነገር ግን፣ ስህተት አንዱ የትምህርቱ አካል መሆኑን አበክረው ይገጻሉ።

በተጨማሪም እነ O' Malley (1990) ችግርን መለየት ለመማሩ ውጤታማነት አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባሉ። ይህንን የቋንቋ ትምህርት አላማ ግብ ለማድረስ በሚደረግ በማንኛውም

እንቅስቃሴ የሚገጥሙ ችግሮች ካሉ በመፈተሽና በማጥራት ለመፍታት የሚዘጋጁበት ብልሃት በመሆኑ መረጃውና ትውረቱ ስሙም ናቸው (O'Malley, 1987)።

ከልዕሸ አእምሮታዊ ብልሃቶች መካከል ሰዋስውን ለመማር ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው የስህተት ምንጮችን መለየትና መገምገም የሚባሉት ናቸው። ለዚህም በመጠይቅ 31 እና 33 ላይ የሚታየውን መረጃ መመልከት በቂ ነው። ይህም በአማካይ 56 (53%) ተማሪዎች መሆናቸውን በሰንጠረዥ ስድስት የሚታየው መረጃ ያረጋግጣል። ተማሪዎቹ የስህተት ምንጭ መለየትና መገምገም የሚባሉትን ብልሃቶች በተሻለ ሁኔታ የሚጠቀሙባቸው መሆኑን የጥናቱ መረጃ አመልክቷል።

በአንጻሩ ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች የአማርኛ ሰዋስውን ለመማር ብዙዎቹ ተጠኚ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ሆነው እንዳልተገኙ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በአማካይ 46 (43%) ያህሉ እነዚህን ብልሃቶች ፍጹም አንጠቀሚባቸውም በማለት መልስ የሰጡ መሆናቸውን የጥናቱ መረጃ አማልክቷል።

በአጠቃላይ በልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች በሰንጠረዥ ስድሰት ከ28 እስከ 33 በቀረቡት ጥያቄዎች መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ለመማር የአዕምሮ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፣ ማደረጀት፣ የሰዋሰው የስህተት ምንጮችን መገምገም እና ግላዊ ድጋፍ ማመቻቸት የስህተት ምንጮችን መለየት የግል ግምገማ ማድረግ ጥያቄዎች የሰዋሰው የመማር ብልሃቶች በተዘውታርነት አብዛኛዎቹ ተጠኚ ተማሪዎች በጭራሽ እንደማይጠቀሙ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን አልፎ አልፎ በብቃት መጠቀም ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ በሰንጠረዥ ስድስት ከተጠኚ ተማሪዎች የተሰበሰበው የመረጃ ትንተና ውጤት አሳይቷል።

### 4.2.2 የስሜት ነኪ ቁጥር ብልሃቶች ጥቅል መረጃ ትንተናና ውጤት

በዚህ ብልሃት ስር ከተራ ቁጥር 34_37 ድረስ የተዘረዘሩ መጠይቆች ለተጠኚ ተማሪዎች ቀርበው ምላሽ እንዲሰጥባቸው ተደርገዋል።

በርግጥ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አንድን የቋንቋ ይዘት በሚማሩበት ጊዜ ለቋንቋው ባህል ካላቸው እንግድነት፣ የቃላት አዲስነት እንድሁም የቋንቋው ስራአት አስቸጋሪነት ወዘተ ለመቋቋም የሚያስችሉት የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች ስጋትን (ጭንቀትን) መቀነስ፣ ራስን ማበረታታትና ውስጣዊ የፍርሃት ግፊቶችን መቆጣጠር ወዘተ ናቸው (Oxford;1990;140)(Oxford, 1990)።

እነዚህን ብልሃቶች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር የሚያስችሉ ስለመሆን አለመሆናቸውን ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ውጤቶች የተገኙ ቢሆንም፣ እያንዳንዱን የመማር ብልሃት ዝርዝር ትንተናና ውጤት ከሰንጠረዥ ሰባት ቀጥሎ በተራ ቁጥራቸው መሰረት ከትውረቶች ጋር እየተነጻጸሩ ቀርበዋል።

*ሠንጠረዥ 7 የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ጥቅል መረጃ*

| ተ.ቁ | ብልሃቶች | የአጠቃቀም ተዘውታሪነት አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፍጹም | | አልፎአልፎ | | በአብዛኛው | | ሁልጊዜ | |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| 34 | በመማር መሳሳት ቢኖርም እራስን ማደፋፈር | 27 | 25 | 55 | 52 | 18 | 17 | 6 | 6 |
| 35 | ከአፍ መፍቻ አቻ የሆኑ መዋቅሮች በማዛናናት ለመማር | 59 | 56 | 31 | 29 | 5 | 5 | 11 | 10 |
| 36 | ግንዛቤ ከፍ እያለ ሲመጣ እራስን ማድነቅ | 55 | 52 | 25 | 24 | 8 | 8 | 18 | 17 |
| 37 | ሰዋስውን ለመማር ከስጋት ነጻ መሆን | 60 | 57 | 19 | 18 | 14 | 13 | 13 | 12 |
| | አማካይ | 50 | 47 | 33 | 31 | 11 | 10 | 12 | 11 |

ጥያቄ 34 ሰዋስውን በመማር ሂደት የሚከሰቱ ስህተቶችን የትምህርት አንዱ አካል አድርጎ መቁጠርና ራስን በማደፋፈር መማር መቻል የሚለውን የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃት የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ለመፈተሽ የቀረበ ነው።

በመሆኑም ይህን ብልሃት አልፎ አልፎ እንጠቀማለን ያሉት 55 (52%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ፣ፍጹም አንጠቀምበትም በማለት የመለሱ 27 (25%) ተጠኚዎች ናቸው። ይህንን

ብልሃት በአብዛኛው የሚጠቀሙት 18 (17%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙበት ያመለከቱት 6 (6%) ተማሪዎች ናቸው።

ከቀረበው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎች በብልሃቶቹ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ነው። ይህውጤት በምዕራፍ አንድ ከቀረቡት ተዛማጅ ጥናቶች ከይርጋ (1997) የጥናት ውጤትና በምዕራፍ ሁለት ከተጠቀሰው የድርሳን ክለሳ ነጥቦች ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል።

ቁጥር 35 አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ከምባትኛ አፍ_ፈት ተማሪዎች ከአፍ መፍቻ ሰዋስው ጋር አቻ የሆኑ መዋቅሮችን በሚያገኙበት ጊዜ ራሳቸውን በማስደሰትና በማዝናናት የመማር ልምዳቸውን ለመፈተሽ የቀረበ መጠይቅ ነው። ለዚህ መጠይቅ በሰጡት መረጃ መሰረት ፍጹም አንጠቀሚበትም ያሉት 59 (56%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት ደግሞ 31(29%) ተማሪዎች ናቸው። ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 11 (10%) ያህል ተማሪዎች ሲሆኑ፣ በአብዛኛው የሚጠቀሙ 5 (5%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው።

ብልሃቱ ሰዋስውን ለመማር ከሚጠቀሙበት መካከል አንዱ ቢሆንም፣ በቁጥር 35 ከቀረበመጠይቅ ተማሪዎች ያላቸው የአጠቃቀም ልምድ እርስ በርሳቸው የሚጣጣሙ አይደሉም። በምዕራፍ ሁለት በተጠቀሱት ድርሳናት ተማሪዎች ለትምህርት የቀረበላቸውን ይዘት በደስታና በመዝናናት ሲማሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ ያብራራል። Oxford (1990; 400) አዝናኝ መጽሓፍትን በማንበብና ፍሬ ነገሮችን ከውስጡ መፈለግ የሚያስችል መለማመጃዎችን በመስጠት ብልሃቱን እንደሚጠቀሙበት የሚያነቃቃ ሊያስፈልግ ይችላል (Oxford, 1990)።

ቁጥር 36 በክፍል ውስጥ የሚሰተው የሰዋስው ትምህርት ግንዛቤ ከፍ እያለ ሲመጣ ራስን ማድነቅ መቻል ወሳኝ በመሆኑ፣ ተማሪዎች ይህንን ብልሃት ተጠቅመው በመማር ደረጃ ያላቸውን ልምድ ለመፈተሽ የቀረበ ነው። በመሆኑም በዚህ ብልሃት ፍጹም አንጠቀሚበትም ያሉት 55 (52%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት ደግሞ 25 (24%) ተማሪዎች ናቸው። ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 18 (17%) ያህል ተማሪዎች ሲሆኑ፣ በአብዛኛው የሚጠቀሙ 8 (8%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው።

ብልሃቱን አዛውትረው ከመጠቀም አኳያ ተግባራዊ ያደረጉት ተማሪዎች ይበዛሉ። ይህ በበኩሉ በክለሳ ድርሳኑ ከተሰጠው የምሁራኑ ማብራርያ አንጻር የሀሳብ መፋለስ የሚታይበት ይመስላል። Oxford 1990እና Stern (1983) ለውጤታማ አፈጻጸሞች ራስን መሸለም፣ ትምህርቱን

በውጤታማነት ለመፈጸም ከሚያግዙ ብልሃቶች መካከል እንደሚጠቀስ አረጋግጧል:: ስለሆነም ለብልሃቱ ተዘውታሪነት የሚያግዙ አሰራሮችን በመማሪያ ክፍል ውስጥ መዘርጋት የሚያስፈልግ ይሆናል (Oxford, 1990; Sternn, 1983)::

ቁጥር 37 አፈቻውን በከምባትኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ይህንን ብልሃት በመጠቀም ደረጃ ያላቸውን ልምድ ለማወቅ የቀረበውን መጠይቅ ፍጹም አንጠቀሚበትም ያሉት 60 (57%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት ደግሞ 19 (18%) ተማሪዎች ናቸው:: በአብዛኛው የሚጠቀሙ 14 (13%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 13 (12%) ያህል ተማሪዎች ናቸው:: በብልሃቱ የተማሪዎች የአጠቃቀም ልምድ ዝቅተኛ መሆኑን መረጃው ያስረዳል:: በብልሃቱ የማይጠቀሙበት ምክንያት የሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ የፍርሃት ስሜት መቆጣጠር አለመቻላቸው ሊሆን ይችላል:: ምሁራን እነ O' Malley (1990)፣ Stern(1983) ፣Oxford (1990) ከስጋት ነጻ መሆን የሚለውን የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃት የሰዋስው ትምህርትን ለመማር ጠቃሚ ከሚባሉት መካከል ሊመደብ የሚችል መሆኑን ገልጿል (O'Malley, 1987; Oxford, 1990; Sternn, 1983):: በመሆኑም በብልሃቱ እንዲጠቀሙበት ማበረታታት ያስፈልጋል::

በሰንጠረዡ ሰባት አጠቃላይ የተማሪዎችን መረጃና የጥናቱ ውጤት ተደራጅቷል::ይሁን እንጂ ወደ ዝርዝር ብልሃቶች ከመግባታችን በፊት በተናጥልና በጥልቅ የዚህን ብልሃት ውጤት ባጭሩ እንመለከታለን:: መረጃው የሚያመለክተው ከስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች በተናጥል ስመረመሩ ራስን ማደፋፈር ሰዋስውን ለመማር ተጨማሪ ብልሃት መሆኑን 79(75%) ተማሪዎች አመልክቷል:: በተጨማሪም በቃለ መጠይቅ የተገኘውም መረጃ ይህንን ውጤት የሚደግፍ ሆኖ ተገግቷል::

ስለሆነም በምዕራፍ ሁለት በድርሳን ክለሳው Oxford (1990;140) እና Stern (1983;411) ከጠቀሱት መረጃ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል (Stern,1983)::

በአንጻሩ በመጠይቁ የቀረቡትን አራት ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶችን ከጠቅላላው አማራጮች አኳያ ስታይ 50 (47%) ያህል ተማሪዎች የማይጠቀሙባቸው መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል::

በአጠቃላይ ከተራ ቁጥር 34_37 የቀረቡት የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ስጋትን መቀነስ፣ ራስን ማበረታታት እና የፍርሃትን ግፊቶችን መቆጣጠር መሆናቸውን (Oxford፣1990: 140-

141) ይገልጻል። ከነዚህ መካከል ራስን ማደፋፈር የሚባለውን ብልሃት ተማሪዎች በአብዛኛው እንደሚጠቀሙበት መረጃው ያመለክታል።

ይሁን እንጂ ሰዋስውን ለመማር ያላቸውን ተዘውታሪነት በተመለከተ አልፎ አልፎ፣ በአብዛኛውና ሁል ጊዜ የሚሉትን አማራጮች በተለያየ ደረጃ በመገልገላቸው ድምር ውጤቱ አመርቂ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ እንዲጠቀሙበት ግፊት ማድረግ ያስፈልጋል።

እነዚህን ብልሃቶች በሚመለከት ብዙዎች ተማሪዎች ያላቸው ልዩ የመማር ብልሃት ብለው የጠቀሱት ነገር የሌለ ቢሆንም፣ ሰዋስው ሲማሩ የሚፈሩ መሆናቸውን፣ ራሳቸውን የማድነቅ ልምድ እንደሌላቸው የገለጹ ተማሪዎች አሉ። ይህም የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃትን የማይጠቀሙ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

### 4.2.3 የማህበራዊ ጥቅል መረጃ ትንተናና ውጤት

በሰንጠረዥ ስምንት ከተራ ቁጥር 38_42 የቀረቡት ማህበራዊ የመማር ብልሃቶች ውስጥ የሚካተቱ መጠይቆች ናቸው። እነዚህ መጠይቆች ለተማሪዎች ተሰጥተው የተገኘውን አጠቃላይ ውጤት ሰንጠረዡ ያመለክታል።

*ሠንጠረዥ 8 የማህበራዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ*

| ተ.ቁ | ብልሃቶች | የአጠቃቀም ተዘውታሪነት አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፍጹም | | አልፎ አልፎ | | በአብዛኛው | | ሁልጊዜ | |
| | | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % | ቁ | % |
| 38 | በሰዋስው ትምህርት የጓደኛን ድጋፍ መጠየቅ | 25 | 24 | 23 | 22 | 39 | 37 | 19 | 18 |
| 39 | ሰዋስውን በመተባበር መማር | 27 | 254 | 21 | 20 | 29 | 27 | 29 | 27 |
| 40 | የመምህራንን ማብራሪያ በመጠየቅ መማር | 33 | 31 | 11 | 10 | 26 | 25 | 36 | 34 |
| 41 | ስህተቶችን በመተባበር ማስተካከል | 19 | 18 | 25 | 24 | 35 | 33 | 27 | 25 |
| 42 | የአፍ_ፈቶችን የመማር ልምድ መከተል | 35 | 33 | 17 | 16 | 32 | 30 | 22 | 21 |
| | አማካይ | 28 | 26 | 19 | 18 | 32 | 30 | 26 | 25 |

ቁጥር 38 የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚገጥማቸውን ችግር ለመፍታት ከሚያስችሉ የማህበራዊ ብልሃቶች አንዱ የጓደኛን ድጋፍ በመጠየቅ መማር መቻል ነው።ይህንን ብልሃት በመጠቀም የመማር ልምዳቸውን ለማወቅ የቀረበውን ይህን መጠይቅ በአብዛኛው የሚጠቀሙ 39 (37%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ፣ ፍጹም አንጠቀሚበትም ያሉት 25 (24%) ተማሪዎች ናቸው። አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት ደግሞ 23 (22%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 19 (18%) ያህል ተማሪዎች ናቸው። ብልሃቱን በአብዛኛውና ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት ተማሪዎች በአንጻራዊነት አብላጫውን የሚይዙ በመሆናቸው ብልሃቱ ተዘውታሪነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ በተጨማሪም በምዕራፍ ሁለት የተጠቀሱት ድርሳናት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ ማህበራዊ ማስተጋብራቸው የራሱን ሚና ይጫወታል።

ማህበራዊ ቋንቋን የመማር ሂደት ከጓደኛ፣ ከምሁራን፣ ከቤተሰብ፣ ከአፍ_ፈት ተማሪዎች ወዘተ ድጋፍ በመጠየቅና በመተባበር የሚከናወን በመሆኑ ለውጤት የሚያበቃ መሆኑን Ellis (1997) ያስረዳሉ። በመሆኑ ብልሃቱ በተማሪዎች ተማራጭ ሆኖ መገኘቱ ተገቢነት ያለውና ይርጋ (1997) "ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች" ይገለገሉባቸዋል ከተባሉ ስድስቱም አይነት ብልሃቶች ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል (ይርጋ, 1997)።

ቁጥር 39 ስለ ቋንቋው ስርአት ከመምህራንና ከጓደኛ ጋር በመተባበር ትንታኔ በመስጠት መማር መቻል የሚለውን ማህበራዊ ቋንቋን የምመማር ብልሃት በተመለከተ ያላቸውን ልምድ ለመፈተሽ ለቀረቡላቸው ጥያቄ በአብዛኛው የሚጠቀሙ 29 (27%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 29 (27%) ያህል ተማሪዎች ናቸው።ፍጹም አንጠቀሚበትም ያሉት 27 (25%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት ደግሞ 21 (20%) ተማሪዎች ናቸው።

ከምሁራን አስተሳሰብ አኳያም ሲገመገም በምዕራፍ ሁለት እንደተጠቀሰው እነ O' malley (1990) የታላሚውን ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ግንዛቤ ለማግኘት፣ ልምድና ሀሳብን ለመለዋወጥ፣ የቋንቋ ነክ ትምህርቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥ፣ ለመማሩ ስርዐት ይረዳ ዘንድ አርዓያ (ሞዴል) ለማግኘት ከተለያዩ ሰዎች በመዋሀድ የመስራት ብልሃቶች ናቸው። ተማሪዎች ይህንን ተግባር እየፈጸሙ የሚማሩ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

ቁጥር 40 ከማህበራዊ ብልሃቶች መካከል አንዱ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ የመምህራንን ማብራሪያ በመጠየቅ መማር መሆኑን ምሁራን ያብራራሉ። የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ስለመጠቀም አለመጠቀም በሰጡት መረጃ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 36 (34%) ያህል ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ፍጹም አንጠቀሚበትም ያሉት 33 (31%) ተማሪዎች ናቸው። በአብዛኛው የሚጠቀሙ 26 (25%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ፣አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት ደግሞ 11(10%) ተማሪዎች ናቸው። ብልሃቱን በአብዛኛውና ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት ተማሪዎች 60 (57%) ያህል ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ 44 (41%) ፍጹም አንጠቀምምና አልፎ አልፎ የሚለውን አማራጭ የመልሱ ናቸው። በመሆኑ ብልሃቱ በተማሪዎች የሚሰራበት ሆኖ ተገኝቷል።

ቁጥር 41 ስህተቶችን ከኅበዝ ተማሪዎችና ከመምህራን ጋር በመተባበር በማስተካከል ለመገንዘብ መቻል ከማህበራዊ ብልሃቶች አንዱ በመሆኑ፣ ይህንን ብልሃት የመጠቀም ልምዳቸውን

ለማወቅ የቀረበ ነው:: በመሆኑም በአብዛኛው የሚጠቀሙ 35 (33%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ፣ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 27 (25%) ያህል ተማሪዎች ናቸው::አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት 25 (24%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ፍጹም አንጠቀሚበትም ያሉት 19 (18%) ተማሪዎች ናቸው:: ከቀረበው መረጃ ማጠቃለል የሚቻለው በአብዛኛውና ሁል ጊዜ የሚጠቀሙበት ተማሪዎች 62 (58%) ስለሆኑ በምዕራፍ ሁለት ከተገለጸው ትውረት ጋር የተጣጣመ ነው::

ቁጥር 42 የአፍ_ፈት ተማሪዎችን ስሜት ለመጋራትና የቋንቋውን ባህል በመከተል መማር የሚለውን ማህበራዊ የመማር ብልሃት የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ሰዋስውን ለመማር ይጠቀሙበት እንደሆነ ለመፈተሽ የቀረበ መጠይቅ ነው:: ለዚህ ብልሃት ከቀረቡት አማራጮች መካከል ፍጹም አንጠቀሚበትም ያሉት 35 (33%) ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ እንጠቀምበታለን ያሉት ደግሞ 17 (16%) ተማሪዎች ናቸው:: በአብዛኛው የሚጠቀሙ 32 (30%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ ሁል ጊዜ እንጠቀምበታለን ያሉት 22 (21%) ያህል ተማሪዎች ናቸው:: ከቀረበው የመጠይቅ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው 51% ያህል ተጠኚዎች በአብዛኛውና ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆኑ፣ 49% ደግሞ አልፎ አልፎ እና በፍጹም የማይገለገሉ ሆነው ተገኝቷል:: ከላይ ስለማህበራዊ ብልሃቶች የከቀረበው መረጃ በምዕራፍ ሁለት ካለው የክለሳ ድርሳን ፍሬ ነገሮች ጋር የተጣጣመ ሆኖ በመገኘቱ በዚህ ጥናት ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የሰዋስው ትምህርትን ለመማር የሚገለገሉባቸው ብልሃቶች ሆነው ተገኝተዋል::

በተጨማሪ የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ዕውቀታችሁን ለማዳበር ጥረት ታደርጋላችሁ? መልሳችሁ "አዎን" ከሆነ ምን አይነት ተግባራትን አከናዎናችሁ? ለሚለው ቃለ መጠይቅ 11 ተማሪዎች እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በአማካይ የተጠቃለለው መረጃ የሚያሳየው78 (74%) ተማሪዎች ማህበራዊ ብልሃቶችን በአብዛኛውና ሁል ጊዜ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በማህበራዊ ብልሃቶች ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ሲማር የሚገጥመውን ችግር መምህሩን፣ ጓደኛውን፣ የታላሚውን ቋንቋ አፍ_ፈት ተነጋሪዎችና ሌሎች ድጋፍ ልያደርጉ የሚችሉ አካላትን በመጠየቅ እርማትና ማስተካከያ እንዲደረግለት በማግባባት ይማራል፡፡ ለምሳሌ፡ተናጋሪው እንዲደግምለት በሌላ አባባል እንዲገልጽለት እንዲብራራለት፣ ሰዋስዋዊ ህጉን በምሳሌ እንዲረዳው በማድረግ ትምህርቱን ይከታተላል፡፡

በአጠቃላይ ማህበራዊ ብልሃቶች ማብራርያ መጠየቅ፣ በመተባበር መማርና የቋንቋውን ባህል መገንዘብ ላይ የሚያጠነጥኑ ሆነው ሌሎችንም ዝርዝር ብልሃቶች ሊያካትቱ የሚችሉ ናቸው። የማህበራዊ ብልሃቶችን ዝርዝር (ከቁጥር 38_42)ትንተና በሚመለከት ከሰንጠረዥ ስምንት ተከትለው በሚመጡት ገጾች በምዕራፍ ሁለት ከሚቀርቡ የክለሳ ድርሳን ነጥቦች ጋር በማመሳከር ለማቅረብ ተሞክሯል።

የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በክፍል ውስጥም ይሁን ውጪ በሚማሩበት ጊዜ ለየት ባለ ሁኔታ የግላቸው የሆኑ የመማሪያ ብልሃቶች እንዲጠቀሙ ለቀረበላቸው ክፍት መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ባይኖርም፣ በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻቸው ጋር በመረዳዳትና መምህራንን በመጠየቅ ትምህርቱን እንደሚማሩ በክፍት መጠይቅ ቦታ ላይ አስራአንድ ተማሪዎች ጽፈዋል። ይህም በዝግ መጠይቅ ከቀረበው ምላሽ ጋር የሚስማማ ከመሆኑም በላይ ከምሁራን ሀሳብ ጋር የሚጣጣም ነው።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃላያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች

## 5.1.ማጠቃላያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አፋቸውን በከምባትኛ ቋንቋ የፈቱ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በሚማሩበት ጊዜ የሚገለገሉባቸውን ሰዋስው ብልሃቶች መተንተን ሆኖ፣ በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ሲማሩ፣ የሚጠቀሙባቸው የመማሪያ ብልሃት አይነቶችን መለየትና ከቋንቋ መማር ብልሃቶች መካከል የትኞቹን አዘውትረው በመጠቀም ትምህርቱን እንደሚከታተሉ መለየት የሚሉ ንዑስ ዓላማዎች አሉት። በመሆኑም ለክፍል ደረጃቸው የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመማር እገዛ የሚያደርጉ ርቱዕ ብልሃቶች (አዕምሮታዊ ትውስታና አካካሽ) እንዲሁም ኢርቱዕ ብልሃቶች (ልዕለ አዕምሮታዊ፣ ስሜት ነኪ_ቁጥጥር እና ማህበራዊ) መሰረት በማድረግ ተተኳሪ ተማሪዎች ሰዋስውን ለመማር በየትኞቹ እንደሚገለገሉና አዘውትረው የትኞቹን እንደሚጠቀሙባቸው ለመለየት ተሞክሯል።

ከመጠይቁ በተገኘው የመረጃ ትንተና ውጤት በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር በተለየ ሁኔታ የሚመርጧቸው ብልሃቶች ያሏቸው መሆኑን መረጃው አመልክቷል። ከእነዚህ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች መካከል ለሰዋስው ትምህርት ይዘት መተግበሪያነት የሚውሉ የተመረጡ ብልሃቶች እንደሚጠቀሙ መረጃው ጠቁሟል። ስለዚህ ተጠኚ ተማሪዎች ዋና ዋና የርቱዕ ብልሃቶች እና ንዑሳን ብልሃቶች በአጠቃላይ ሲታይ የአጠቃቀም ደረጃቸው በእያንዳንዱ የመማር ብልሃቶች ዝቅተኛ መሆኑን የጥናቱ የትንተና ውጤት መረጃ አሳይቷል።

## 5.2. መደምደሚያ

ሀ) የርቱዕ የመማር ብልሃቶች

1 አዕምሮታዊ የመማር ብልሃቶች በሚመለከት፡ ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስውን ለመማር የሚገለገሉባቸው ብልሃቶች በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ የሚሰሩ መልመጃዎችን እና ድግግሞሽ የበዛበት ልምምድ የሚመርጧቸው የመማር ብልሃቶች መሆናቸውን መረጃው አመልክቷል። ከዚህ በተጨማሪ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን 51 (48%) ተጠኚ ተማሪዎች በተለያየ ደረጃ በሚገኙ የአጠቃቀም እርከኖች የሚገለገሉባቸው መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል። እነዚህ

ብልሃቶች ቋንቋን ለመማር ቀጥተኛ አስተዋጽዖ ያላቸው ናቸው። ተማሪዎች የቀደመውን ዕውቀታቸውን ከአሁኑ ትምህርት ጋር እያስተሳሰሩ መማር፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን ለታላሚው ትምህርት መጠቀም፣ ይዘቶችን ማቧደን፣ቃላዊ ጥናትን መጠቀም ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው። ይህ ግኝት ከምዕራፍ ሁለት ከቀረበው የድርሳን ክለሳ ትውረቶች ጋር ስነጻጸር የሚስማማ ሆኖ አልተገኘም።

2 የየማህደር ትውስታ ብልሃቶች በሚመለከት፡ የቋንቋ ተማሪዎች የትውስታ ብልሃቶችን የሚገለገሉባቸው የተማሩትን በአጭርና በረጅም ጊዜ የትውስታ ማህደር በማከማቸት፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አስታውሰው ለመጠቀም ነው። ከእነዚህም መካከል ማስታወሻ መጻፍ፣ አዕምሮአዊ ምስል መፍጠር፣ ልዩ ልዩ ምልክቶችን መጠቀም፣ የአፍ መፍቻና የሁለተኛ ቋንቋ መዋቅሮችን በቃል ወይም በጽሑፍ ለመሸምደድ መሞከር ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው። ከትውስታ ብልሃቶች መካከል በተማሪዎች ተዘውትረው ለሰዋስው ትምህርት መማሪያ የሚጠቀሙባቸው መኖራቸውን መረጃው ጠቁሟል።

የመጀመሪያዎቹ ልዩ ልዩ ምልክቶችን በመጠቀም የሰዋሰው ይዘቶችን የሚማሩባቸው መንገዶች ሲሆኑ፣ሁለተኞቹ ማስታወሻ በመጻፍ የሚማሩባቸው ናቸው።

አጠቃላይ ውጤቱን ስንመለከተው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማህደር ትውስታ ብልሃቶችን በብቃት የሚጠቀሙባቸው ሆነው አልተገኙም። ተማሪዎች የተማሩትን የትምህርት ይዘት በአእምሯቸው አከማችተው አስፈላጊው ጊዜ በማውጣት ለመጠቀም ካልቻሉ በተግባቦትም ሆነ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች (ለምሳሌ በፈተና ጊዜ) የቋንቋውን መዋቅሮች መጠቀም ሊያዳግታቸው ይችላል።

3 የአካካሽ ብልሃቶች በሚመለከት፡ በዚህ ምድብ ውስጥ ተማሪዎች የታላሚው ቋንቋ መዋቅሮች በሚጠፉበት ጊዜ በቀልጣፋ ሁኔታ ለመሙላት የሚያስችል ብልሃቶች ናቸው። ለምሳሌ ምትክ የሚሆኑ መዋቅሮችን ከአፍ መፍቻ ቋንቋ በመፈለግ ማተካካት፣የጠፈ መዋቅርን አፍ ላይ ማጉላላት ወይም ለተወሰነ ጊዜ በዝምታ መተው፣ ቋንቋ አልባ ፍንጮችን ለመጠቀም መሞከር ወዘተ ናቸው። በተናጠል ከአካካሽ ብልሃቶች መካከል ለአቻ መዋቅሮች ምትክ መፈለግ እና የሚከብዱ መዋቅሮችን በዝምታ በማለፍ ድጋፍ መጠየቅ በተማሪዎች ተማራጭ የሰዋስው መማር ብልሃቶች መሆናቸውን መረጃው አመልክቷል።

አጠቃላይ የአካካሽ ብልሃቶችን ጥቅል ግኝት ስንመለከት ለአማርኛ ሰዋስው ትምህርት መማሪያነት ተማሪዎች በብቃት የማይጠቀሙባቸው መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል።

ለ) የኢ-ርቱዕ የመማር ብልሃቶች

1 ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች በሚመለከት፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በልዕለ አእምሮታዊ ብልሃት ታግዘው ሲማሩ በዕቅድ የሚመሩ፣ ለትምህርቱ ትኩረት የሚሰጡና መማራቸውን የሚገመግሙ ሊሆኑ እንደሚገባቸው Oxford (1990:137) ይገልጻል። በአንጻሩ ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶችን በሚመለከት የተገኘው መረጃ በጥቅሉ ሲታይ የአማርኛ ሰዋስውን ለመማር ብዙዎች ተጠኚ ተማሪዎች በብቃት የሚጠቀሙባቸው ሆነው እንዳልተገኙ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

ከልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች መካከል በተናጠል ሲታይ ሰዋስውን ለመማር ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው የስህተት ምንጮች መለየትና መተንተን ተመራጭ ሰዋስው ይዘት መማር ብልሃቶች መሆናቸውንጥናቱአሳይቷል።ተማሪዎቹ ለሰዋስው ትምህርታቸው የመረጧቸውን ብልሃቶች (የስህተት ምንጭ መለየት እና መገምገም የሚባሉትን) ብልሃቶች የሚጠቀሙ መሆኑን የጥናቱ መረጃ አመልክቷል።

2 ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶችን በሚመለከት፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የታላሚውን ትምህርት ይዘት በሚከታተሉበት ጊዜ የሚሰማቸውን የስሜት መረበሽ ለመቆጣጠር የሚያስችሏቸው ራሳቸውን የሚያበረታቱባቸው፣ ከስጋት ነጻ የሚሆኑባቸውና የፍርሐት ስሜትቶቻቸውን የሚቆጣጠሩባቸው ብልሃቶች ናቸው።

ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሐቶች በተናጠል ሲመረመሩ ራስን ማደፋፈር የሚባሉት የመማር ብልሐቶች ሰዋስውን ለመማር በተማሪዎች ተማራጭ ብልሃት መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል።

በአንጻሩ በመጠይቁ የቀረቡትን የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶችን ጥቅል ውጤት 53% በላይ ተጠኚ ተማሪዎች የማይጠቀሙባቸው መሆናቸውን መረጃው ሲያመለክት፣ይህም ተማሪዎቹ አነስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆን ነው።

በርግጥ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አንድን የቋንቋ ይዘት በሚማሩበት ጊዜ ለቋንቋው ባህል ካላቸው እንግዳነት፣ የቃላት አዲስነት እንዲሁም የቋንቋን ስርዓት አስቸጋሪነት ወዘተ ለመቋቋም የሚያስችሉት የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች ስጋትን (ጭንቀትን) መቀነስ፣ ራስን ማበረታትና ውስጣዊ የፍርሃት ግፊቶችን መቆጣጠር መቻል ወዘተ

ናቸው።ስለሆነም በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች ላይ ጫና ሊያሳርፉ የሚችሉ ማነኛውንም ግፊቶች መቆጣጠር የሚያስፈልግ መሆኑን መረጃው ጥቆማ ይሰጣል።

3 ማህበራዊ ብልሃቶች በሚመለከት፡- ማህበራዊ ብልሃቶችን በሚመለከት መረጃ እየተሰበሰበ በመተባበር መማር፣ ማብራሪያ በመጠየቅ መማርና የቋንቋውን ባህል በመከተል መማር የሚሉት ናቸው። በማህበራዊ ብልሃቶች ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ሲማር የሚገጥመውን ችግር መምህሩን፣ ጓደኛውን፣ የታላሚውን ቋንቋ አፍፊት ተናጋሪዎችና ሌሎች ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ አካላትን በመጠየቅ እርማትና ማስተካካያ እንዲደረግለት በማግባባት ይማራል። ለምሳሌ ተናጋሪው እንዲደገምለት፣ በሌላ አባባል እንዲገልጽለት፣እንዲብራራለት፣ ሰዋስዋዊ ህጉን በምሳሌ እንዲያስረዳው በማድረግ ትምህርቱን ይከታተላል። ተማሪዎች ከዚህ በላይ ማህበራዊ ብልሃቶችን የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ሆነው ተገኝተዋል።

በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት በዝርዝር ከተገለጹት የOxford (1990)፣ Ellis (1997)፤ Stern (19883)፤እና O'Malley (1990) ካነሷቸው ፍሬ ነገሮች ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ ተጠኚ ተማሪዎች ጽሑፍ መጠይቁና ቃለ መጠይቁ በሰጡት መረጃ መሰረት ከምባትኛ አፍ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማሩ ማህበራዊ ብልሃቶች ሰዋስው ለመማር የመጀማሪያውን ቦታ የሚይዙ ሆነው ተገኝተዋል። በአጠቃላይ በዚህ ጥናት መሰረት አዕምሮታዊ ብልሃቶች መካከል መልመጃዎችን መስራትና ድግግሞሽ የበዛበት የቋንቋ ክንውን የትውስተ ብልሃቶች ከሚባሉት ልዩ ልዩ ምልክቶችን መጠቀምና ማስታወሻ መጻፍ እንዲሁም ከአካካሽ ብልሃቶች መካከል አቻ ምትክ መፈለግ በዝምታ አልፎ ድጋፍ መጠየቅ በብቃት የሚማሩባቸው የርቱዕ ብልሃቶች አካላት ሆነው ተገኝተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ከልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች መካከል የስህተት ምንጮችን መለየትና መገምገም፣ ከስሜት ነክ_ቁጥጥር ብልሃቶች መካከል ለመማር ራስን ማደፋፈር የሚያስችሉትን እንዲሁም ከማህበራዊ ብልሃቶች ማብራርያን መጠየቅ በመተባበር መማርና የቋንቋውን ባህል በመከተል መማር በብዛት ትምህርታቸውን የሚከታተሉባቸው የኢርቱዕ ብልሃቶች ንዑሳን አካላት ሆነው ተገኝተዋል።

ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ ቋንቋን ለመማር በቀላሉ የሚረዷቸውን ርቱዕ ብልሃቶች አላመጠቀማቸው የቋንቋን ስርዓት የሚያመለክተውን ሰዋስውን በብልሃቶቹ ታግዞ መማር አለመቻል በትምህርቱ ሂደት የበኩሉን አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም።

## 5.3 የመፍትሄ ሀሳብ

ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በከምባትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የአማርኛን ሰዋስውን ለመማር ማህበራዊ ብልሃት የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር በተማሪዎቹ የሚዘወተር የመማር ብልሃት መሆኑ ስረጋገጥ አዕምሮታዊ፣ ትውስታ፣ አካካሽ፣ ልዕለ አዕምሮታዊና ስሜት ነክ_ቁጥጥር በተማሪዎች በበለጠ ተዘውታሪ ሆነው አልተገኙም።

ማህበራዊ መማር በጋራ እየተወያዩ መማርን የሚያሳይ ሲሆን በትብብራዊ መማር ተግባራት አበጥሮ መማር፣ የማሰብና የማሰላሰል ክሂል እና የተግባቦት ክሂሎትን ያዋህዳል። ማህበራዊ መማር ተማሪዎቹ ከሌሎች ጋር በትብብር ለመስራት ይነቃቃሉ። የቡድን ስኬት የግለሰቦች ስኬት የሚሆንበት አጋጣሚ ስለሚኖር ብሩህ እና ኀበዝ ተማሪዎች ደከም ያሉትን ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዟቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች ተማሪዎች እንደት እንደሚያስተውሉና እንደሚያስቡ፣ ችግሮችን እንደት እንደሚፈቱና ከሌሎች ሰዎች ጋር እንደት መተባበር እንደሚቻል ይማራሉ። መማርን ትርጉም ያለውና ሳቢ ለማድረግ መምህራን የተለያዩ ተግባራትን በትብብራዊ መማር ብያደራጁ፣ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የሰዋስው እውቀታቸውን በብቃት በማዳበር የተግባቦት አቅማቸውን ለማበልጸግ የሚችሉት የትምህርት ሂደቱ ዋና ተዋናህ ሆነው ተማሪዎች መሳተፍ ሲችሉ ነው። መምህራን ትንሽ ድጋፍና ጥቆማ በማድረግ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው የሚማሩበትን መላ (ሰዋስው የመማር ብልሃቶች) ማስገንዘብ ቢችሉ ብዙዎቹ ተማሪዎች በምሁራን የተጠቀሱትን የመማር ብልሃቶች (በጥናቱ ከተረጋገጡ የተወሰኑ ርቱዕና ኢርቱዕ ብልሃቶች በስተቀር) እንደማያውቋቸውና እንደማይገለገሉባቸው፣ እንዲሁም የራሳቸው የሆነ ግላዊ ብልሃት የሌሏቸው መሆናቸው በጥናቱ ውጤት በግልጽ ታይቷል። ስለሆነም ተማሪዎች የአማርኛ ሰዋስውን ለመማር ችግር ሊገጥማቸው ይችላል። ስለዚህም አጥኚው የመፍትሔ ሀሳቦች ሊሆኑ ይችላሉ ያላቸውን የሚከተሉትን የመፍትሔ ሀሳቦችን አቅርቧል።

1 የቋንቋን ትምህርት በብቃትና በቀላሉ ለመማር የሚያገልግሉ ርቱዕና ኢርቱዕ ብልሃቶችን ተማሪዎች በብዛት ሲጠቀሙባቸው አልታዩም። ነገር ግን እነዚህ ብልሃቶች የሁለተኛ ቋንቋ

ተማሪዎች በመማር ማስተማርም ይሁን በተግባቦት ሂደት አስፈላጊ በመሆናቸው ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉበትን መንገድ መምህራን ጥቆማ ቢሰጡ፣

2 የትምህርት ባለሙያዎች ስራአተ ትምህርትን፣ መርሃ_ትምህርትንና መማሪያ መጽሐፍትን በሚያዘጋጁበት ጊዜ በእነዚህ የትምህርት ሰነዶች የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በመማር ብልሐቶች አማካይነት በቀላሉ ተማሪዎች ሊማሩባቸው የሚችሉትን ብልሃቶች ጥቆማ ቢሰጡ፣

3 የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ሊያሻሽል በሚችል መልኩ ራሳቸው ኃላፊነት ወስደው በግል ጥረታቸው በመማሪያ ክፍልም ሆነ ውጪ የሚማሩበት ሁኔታ እንዲመቻች ብልሃቶችን በሚገባ የማስተዋወቅ ስራ ቢከናወን፣

4 ተማሪዎች ሰዋስውን ለመማር የሚያገለግሉ ብለው በመረጧቸው ብልሃቶች እንዲገለገሉ የሚጋብዙ የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ቢካተቱ፣

5 ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ መምህራን ልዩ ልዩ ብልሃቶችን ራሳቸው ተማሪዎች እንዲፈጥሩ ቢያበረታቱ፣ በየጊዜው በየትኛው ብልሃት እየተጠቀሙ እንደሆነ እየለዩና ክትትል እያደረጉ የመማር ሂደቱን የተመቻቸ ቢያደርጉ፣

6 በመጨረሻም ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ መማር የጀመሩት ከሶስተኛ ክፍል መሆኑን በመጠይቁ ከሞሉት ግላዊ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል። በዚህ የተነሳ አማርኛ የቀረበላቸውን የጽሑፍ መጠይቅ አንብበው ለመረዳት እንዲሁም ለክፍት መጠይቆቹ በጽሑፍ ሀሳባቸውን ለመግለጽ ችግር ሊገጥማቸው ይችላል። ስለሆነም በዚህ መስክ ጥናት ለማድረግ የሚፈልጉ አካላት መጠይቁን በተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ በማዘጋጀት መረጃ በመሰብሰብ ያለውን ተላውጦና ሌሎችንም በመጠቀም ሊጠና የሚገበው ዘርፍ ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ በመማር ብልሃቶች አማካይነት ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርታቸውን በሚገባ እንዲከታተሉ ለማስቻል ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል የሚል እምነት አለኝ።

# ዋቢ ጽሑፎች

በላይነሽ ደነቀ፡፡ (2002)፡፡ ‹‹በኦሮሚያ ክልል በኢሉባቡር ዞን የመቱ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶች ፍተሻ›› በአዲስ አበበ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ በማስተማር (TeAM) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፡፡

ባየ ይማም፡፡ (2000)፡፡ የአማርኛ ሰዋስው የተሻሻለ ሁለተኛ እትም፣ እሌን. ማ.ኃ.የተ.የግ.ማህበር

ንጋቱ አሰፋ፡፡ (2000)፡፡ "በሲዳመኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው የመማር ብልሃቶች ምርመራ" በቋንቋዎች ጥናትና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ በማስተማር (TeAm) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

አፈወርቅ ይስሃቅ፡፡ (2008)፡፡ "በጋሞ ጎፋ ዞን የሚማሩ አፈ ፈት እና ኢ አፈፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላት የመማር ብልሃቶች ፍተሻ" በቋንቋዎች ጥናትና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ በማስተማር (TeAm) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

ወይንሸት ታደሰ፡፡(2011)፡፡ በሲዲማ ዞንዲራ ወረዳ ቀባድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቃላት ማስተማሪያ ብሌሃቶች የተማሪዎችን የቃላት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር ያላቸው አስተዋጽኦ (ሲዲምኛ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት).

ይርጋ አለሙ፡፡(1993)፡፡አፈቸውን በከፍኛ የፈቱ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች አማርኛን ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ቋንቋ መማር ብልሃቶችንና የመምህራን ግንዛቤ አሰሳ አዲስ አበበ ዩኒቨርሲቲ

ጌታሁን አማረ፡፡(1990)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ አ.አ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት

_________(2011)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡* የተሻሻለ ሁለተኛ እትም፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢ.ኢ ማተሚያ ቤት።

Abdullaev, Z. K. (2021). Second language learning: Issues and implications. Asian Journal of Multidimensional Research, 10(4), 824-827.

Al Abri, A., Al Seyabi, F., Al Humaidi, S., & Hasan, A. H. (2017). Grammar learning strategies in Omani EFL classes: Type and relation to student proficiency. Journal of Studies in Education, 7(2), 151-166.

Algeo, J. (2006). British or American English?: a handbook of word and grammar patterns: Cambridge University Press.

Allen, E. D., & Valette, R. M. (1977). Classroom Techniques: Foreign Languages and English as Second Language.

Alqahtani, M. (2015). The importance of vocabulary in language learning and how to be taught. International journal of teaching and education, 3(3), 21-34.

Azizi, M., & Zamaniyan, M. (2013). The relationship between spiritual intelligence and vocabulary learning strategies in EFL learners. Theory & Practice in Language Studies, 3(5).

Batstone, R. (1994). Grammar.Oxford: Oxford University Press.

Bornay, N. (2011). Explicit strategy training in vocabulary learning for beginning Spanish students. FULGOR: Flinders University Languages Group Online Review, 4(3).

Brown. D. (1994). Principles of Languages Learning. Cambridge University Prentice Hall. Regents.

Brown. (2002). strategies for success. a practical guide to learning English.addison wesley longman Inc.

Channell, J. (1988). Psycho linguistic consideration in the study of vocabulary acquisition in Carter, R. and M. McCarthy (eds). Vocabulary and Language Teaching. London: Longman.

Chomsky. N. (1957). Syntactic Structures the Village Teraching. Cambridge: CUP.

Chung, T. M., & Nation, P. (2003). Technical vocabulary in specialised texts.

Cook. V. (2001). Second Language Learning and Language Teaching (3rd ed). New York: Oxford University Press.

DeKeyser, R. M. (1995). Learning second language grammar rules: An experiment with a miniature linguistic system. Studies in second language acquisition, 17(3), 379-410.

Delilu, E. A. (2007). Reading comprehension learning skills from reading Related to comprehension. The Ethiopian Journal of Higher Education, 4(2), 37-69.

Ellis, R. (1989). Classroom Learning Styles and Their Effect on Second Language Acquisition: A Study of two learners system, 17(2), 249-262.

Ellis, R. (1997). Second Language Acquisition and Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Hakan, K., Aydin, B., & Bulent, A. (2015). An investigation of undergraduates' language learning strategies. Procedia-Social and Behavioral Sciences, 197, 1348-1354.

Harmer, J. (1986). Teaching and Learning Grammer. London: Longman.

Harris, D. P. (1969). Testing English as a Second Language.

Hauptman, P. C. (2000). Some hypotheses on the nature of difficulty and ease in second language reading: An application of schema theory. Foreign Language Annals, 33(6), 622-631.

Hill, A. O., & Hill, A. I. (1986). Mother tongue, Father time: a decade of linguistic revolt (Vol. 389): Indiana University Press.

Hulstijn, J. H. (2001). Intentional and incidental second language vocabulary learning: A reappraisal of elaboration, rehearsal and automaticity: na.

Kemp, C. (2007). Strategic processing in grammar learning: Do multilingual use more strategies? International Journal of Multilingualism, 4(4), 241-261.

Lee, S. (2007). Vocabulary learning strategies of Korean university students: Strategy use, vocabulary size, and gender. ENGLISH TEACHING, 62(1), 149-169.

López-Jiménez, M. (2014). A critical analysis of the vocabulary in L2 Spanish textbooks.

Lukėnienė, R. (2010). Negotiating of Meaning: Vocabulary Comprehension and Acquisition through Reading Medium.

Lyons. (1968). Introduction to Theorotical Lingustics. Cambridge: Cambridge Unversity Press.

Mahdavi, M. (2014). An Overview: Metacogination in Education. International Journal of Multidiscplinary and Currrnt Research, 2(6), 529-535.

Mahdavi, S., Rahnamayan, S., & Deb, K. (2018). Opposition based learning: A literature review. Swarm and evolutionary cxomputation, 39, 1-23.

Millar, R. M. (2015). Trask's historical linguistics: Routledge.

Miller, S., & Fox, H. (1994). Automatic grammar acquisition. Paper presented at the Human Language Technology: Proceedings of a Workshop held at Plainsboro, New Jersey, March 8-11, 1994.

Munoz, A., Gallardo, J. C., & Alavarez, I.A. (2010). Improving N-Gram Linguistic Steganopraphy based on templates. Paper presented at the 2010 International Conference on Security and Crytography (SECRYPT).

Nation, P. (2003). The role of the first language in foreign language learning.
Asian EFL Journal, 15. http://www.asian-efl-journal.com/

Nikoopour, J., Salimian, S., Salimian, S., & Farsani, M. A. (2012). Motivation and the choice of language learning strategies. Journal of Language Teaching and Research, 3(6), 1277.

Nguyễn, T. T. H. (2008). Learner stategies and language learning.*VNU Journal of Foreign Studies, 24*(4).

O'Dell, F., Read, J., & McCarthy, M. (2000). Assessing vocabulary. Cambridge：
Cambridge university press.

O'Malley, J. M. (1987). The Effects of Training In the Use of Learning Strategies on Acquiring English as a Second Lan gu age', In Wenden, A. and J. Rubin (eds), Learner Strategies in Language Learning. New York: Prentice Hall International.

O'Malley, J. M. and Chamot A.U. (1990). Learning Strategies in Second Language Acquisition. New York: cup.

Oxford. (1990). Language Learning Strategies: What Every Teacher Should Know. New York: Newburg House publishers.

Oxford, R. L., Rubin, J., Chamot, A. U., Schramm, K., Lavine, R., Gunning, P., & Nel, C. (2014). The learning strategy prism: Perspectives of learning strategy experts. System, 43, 30-49.

Oxford, R. L., & Scarcella, R. C. (1994). Second language vocabulary learning among adults: State of the art in vocabulary instruction. System, 22(2), 231-243.

Pérez, A. S., & Ruiz, R. M. M. (2007). Research on second language vocabulary acquisition and learning: An introduction. IJES, International Journal of English Studies, 7(2).

Raimes, A. (1991). Out of the woods: Emerging traditions in the teaching of writing. TESOL Quarterly, 25(3), 407-430.

Richards, J. C and T. S Rodgers. (1995). Approach and Methods in Language Teaching. New York. Cambridge University Press.

Rubin, J. (1987 ). 'Learner strategies: Theoretical Assumption, Research History and Typlogy' in Wenden, A and J. Rubin (eds), Learner strategies in Language Learning. UK. Prentice Hall International.

Rutherford, W. E. (2014). Second language grammar: Learning and teaching. London: Routledge.

Sternn. (1983).) Fundamental Concept of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Tılfarlıoğlu, F., & Yalçın, E. (2005). An analysis of the relationship between the use of grammar learning strategies and student achievement at English preparatory classes. Journal of Language and Linguistic Studies, 1(2), 155-169.

Ur, p. (1988). Grammer Practice Activities. Cambridge: cup.

Woods, D. (1991). Teachers' interpretations of second language teaching curricula. RELC Journal, 22(2), 1-18.

Zhongganggao, D. (2001). SECOND LANGUAGE LEARNING AND THE TEACHING OF GRAMMAR [1]. Education, 122(2).

Zybert, J. (2005). Another learning strategy?. Poland: University of Warsaw.

## አባሪ 1

## ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋና ሥነ_ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

ውድ ተማሪዎች!

በመጀመሪያ ጊዜያችሁንና እውቀታችሁን ሳትሰስቱ ይህን መጠይቅ ለመሙላት ስለተባበራችሁኝ አመሰግናለሁ። በመቀጠል የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በ2015ዓም፣ ቀዕላማ፣ አንጋጫና ፉናሙራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ትምህርት ቤቶች ውስጥ ዘጠነኛ ክፍል ከምባትኛ አፍ-ፈት የሆናችሁተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ስትማሩ የምትገለገሉባቸውን ሰዋስው የመማሪያ ብልሃቶች በሚመለከት መረጃ ለመሰብሰብ ነው። እናንተ የምትሰጡት እውነተኛ መረጃ ለዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ ወሳኝነት ስላለው ከልብ ሆናችሁ እንድትሞሉት አደራ እያልኩ፣ የሚትሰጡት መረጃ ከዚህ አገልግሎት ውጪ ሌላ ለምንም ዓላማ የማይውል መሆኑን ቃል እገባለሁ። በመጠይቁ ላይ ስማች ሁን መፃፍ አያስፈልግም።

መመሪያ አንድ፦ የሚከተሉት ግላዊ ማንነታችሁን የሚመለከቱ መረጃዎች ናቸው። እነዚህን መረጃዎች ለመሙላት በክፍት ቦታዎቹ ላይ የ"X" ምልክት በማድረግ አመልክቱ።

1. የትምህርት ቤቱ
   ስምቀዕላማ_______________አንጋጫ_______________ፉናሙራ_______________
2. አፍየፈታችሁበትቋንቋከምባትኛ_______________ አማርኛ____________¨ሌላ_ከሆነ
   _____________
3. ፆታወንድ______________ሴት______________

መመሪያ ሁለት፦ ሰዋስውን ለመማር የሚትገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶች በተመለከተ የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ስለሆናም "እነዚህን ብልሃቶች ለምን ያህል ጊዜ ትጠቀሙባቸዋላችሁ?" ለሚለው ጥያቄ በአረፍተ ነገሮቹ ፊት ለፊት በሚገኙት በቁጥሮቹ ትክክል ለተሰጡ አማራጮች የ"X" ምልክት በመድረግ መልሱ።

## ሠንጠረዥ 9 የጽሑፍ መጠይቅ

| ተ.ቁ | ክፍል አንድ አዕምሮታዊ ብልሃቶች | እነዚህን ብልሃቶች በምን ያህል ጊዜ ትጠቀሙባቸዋላችሁ? | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በፍጹም አልጠቀምም | አልፎ አልፎ ብቻ | አንዳንድ ጊዜ | ሁል ጊዜ |
| 1. | አዳዲስ የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ፡- አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) የሚማረው ከቀዳሚው የሰዋስው እውቀቴ ጋር በማስተሳሰር ነው | | | | |
| 2. | አዳዲስ የሰዋስው መዋቅሮችን (ለምሳሌ፡- አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) የሚማረው በዓይነታቸው በማቧደንና በማመሳሰል ነው (ለምሳሌ፡- ስሞችን በስም ቃል ክፍል፣ግሶችን በግስ ቃል ክፍል ወዘተ) | | | | |
| 3. | አዳዲስ የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ፡- አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) የሚማረው ከአፍ መፍቻ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቋንቋዬ የሰዋሰው መዋቅሮች ጋር እያወዳደርኩ ነው:: | | | | |
| 4. | አዳዲስ የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ፦ አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ስያጋጥሙኝ ትርጉማቸውን ለመረዳት ከምስሎች ጋር ለማገናኘትና ለመገንዘብ እሞክራለሁ:: | | | | |
| 5. | አዳዲስ የሰዋስው ስርዓቶችን (ለምሳሌ፦ አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ስያጋጥሙኝ የቃል ክፍሎቻቸውን ለማጥናት እሞክራለሁ:: | | | | |
| 6. | በከምባትኛ ቋንቋ የማውቀው ሰዋስው የአማርኛን ቋንቋ ሰዋስው ለመማር እረድቶኛል:: | | | | |
| 7. | መምህሬ ስለ አንድ የሰዋስው ህጎች (ለምሳሌ፦ አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) የሚያደርጉትን ገለጻ ካልተረዳሁት ደጋግመው እዲያብራሩልኝ እጠይቃለሁ:: | | | | |
| 8. | መምህሬ አዲስ የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ፦ አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ሲያስረዱ ማስታወሻ በመጻፍ እከታተላለሁ (ለምሳሌ፦ ትርጉሙንና አጠቃቀሙን በመጻፍ ለመገንዘብ እሞክራለሁ):: | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9. | አዲስ የሚማረውን የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ:- አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ለመጻፍ አፍ መፍቻ ቋንቋዬን እጠቀማለሁ:: | | | | |
| 10. | ሰዋስዋዊ ፍሬ ነገሮችን ለመለየት ልዩ ልዩ ዘዴዎችን (ለምሳሌ:- በማቅለም፣ ከስራቸው በማስመር፣ እጠቀማለሁ:: | | | | |
| 11. | የሚማራቸውን የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ:- አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ለመረዳት እንዲመቸኝ ግራፎችን፣ ሰንጠረዦችን፣ ወዘተ እጠቀማለሁ:: | | | | |
| 12. | መምህሬ የሰዋስው ስህተቶቼን ሲያርሙልኝ ትክክለኛውን ቅርፅ ደጋግሜ አስተካክላለሁ:: | | | | |
| 13. | በንግግር ወይም በጽሑፈት ውስጥ አዲሱን የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ:-አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ለመለማመድ እሞክራለሁ<br>(ለምሳሌ:- ድርሰት፣ ደብዳቤ፣ ልዩ ልዩ ማስታወሻዎችን ወዘተ) በመፃፍና በንግግር እለማመዳለሁ:: | | | | |
| 14. | በመኖሪያ ቤቴ የሰዋሰው መልመጃዎችን እሰራለሁ:: | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክፍል ሁለት፦ የማህደር ትውስታ ብልሀቶች | | | | |
| 15. | አዲስ የተማርኳቸውን ሰዋስዋዊ መዋቅሮች ለመሸምደድ እንድችል በተደጋጋሚ በቃሌ መላልሼ እመላልሳቸዋለሁ። | | | | |
| 16. | አንድ ወይም ሁለት አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ በተማርኩት ሰዋስዋዊ ህግ መሰረት መዋቅራቸውን ለማስታወስ እሞክራለሁ። | | | | |
| 17. | በማንኛውም የማዳመጥ ወይም የማንበብ ተግባር ውስጥ አዲሱን ሰዋስዋዊ መዋቅር ለማስታወስ እሞክራለሁ። | | | | |
| 18. | የተማርኩትን የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ፡- አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ሁልጊዜ እከልሰዋለው። | | | | |
| 19. | ስለ አዲሱ የሰዋስው ትምህርቶች(ለምሳሌ፡-አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖረኝ ወይም በሚገባ ግልፅ እንዲሆንልኝ በማሰብ የሰዋስው መጻህፍት አነባለሁ። | | | | |
| 20. | የሰዋስው ህጎችን (ለምሳሌ፡- አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) በተማርኩባቸው ደብተር፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መማሪያ መጻሕፍት፣ ወዘተ ላይ ቦታዎቹን ምልክት በማድረግ ለማስታወስ እሞክራለሁ:: | | | | |
| 21. | አዲስ የተማርኩትን የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ፡- አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ከአገባቡ አንፃር በመተንተን ለማስታወስ እሞክራለሁ:: | | | | |
| 22. | የቀደመ የሰዋስው እውቀቴን ከአዲሱ ሰዋስው ትምህርት ጋር በማገናዘብ ሰፊ ሀሳብን ለመግለጽ የሚያስችሉ አረፍተ ነገሮችን ለመመስረት እጠቀምበታለሁ:: | | | | |
| 23. | የተማርኩትን ለማስታወስ እንዲመቸኝ በሚገባኝ መንገድ አጫጭር ማስታወሻዎችን በመጻፍ እይዛለሁ:: | | | | |
| | ክፍል ሶስት፦ አካካሽ ብልሃቶች | | | | |
| 24. | በምናገርበት ወይም በምጽፍበት ጊዜ የምጠራጠረው የሰዋስው መዋቅር ቢኖር ሌሎች አማራጭ መዋቅሮችን በመተካት እጠቀማለው:: | | | | |
| 25. | ስናገር ወይም ስጽፍ የሚጠፉብኝን የሰዋስው መዋቅሮች (ለምሳሌ፡-አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) በጅምር በመተው ወይም ውስን ድምፆችን በመጥራት ሌሎች ሰዎች እንዲያስተካክሉልኝ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ድጋፍ እጠይቃለሁ፡፡ | | | | |
| 26. | በምጽፍበት ጊዜ የሚጠፉብኝን ሰዋስዋዊ መዋቅሮች በአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ለማስታወስ አቅጣጫየን እቀይራለሁ፡፡ | | | | |
| 27. | አዳዲስ የሰዋስው ደንቦች (ለምሳሌ፡- አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ለንግግር ስገለገል እየጠፉ ካስቸገሩኝ ማቅማማትን ወይም ለውስን ጊዜ ዝምታን እመርጣለሁ፡፡ | | | | |
| | ክፍል አራት፡ ልዕለ አፅምሮታዊ ብልሃቶች | | | | |
| 28. | አዲስ የተማርኳቸውን ሰዋሰዋዊ ስርአቶችን በምን አይነት አውድ ውስጥ ልጠቅምባቸው እንደምችል ቅድመ ዝግጅት አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 29. | መማሪያ ክፍል ከመግባቴ በፊት በሰዋስው ትምህርትነት የቀረቡ ይዘቶችን ቀድሜ አነባቸዋለሁ፡፡ | | | | |
| 30. | በጣም የሚከብደኝን የሰዋስው ትምህርት በመለየት በራሴ ጥረት ለማሻሻል እሰራለሁ፡፡ | | | | |
| 31. | መምህሬ የሚሰጡኝን የቤትና የክፍል ስራዎች በጽሁፍ ስመልስ ስህተት የሆነብኝን እንደገና በመከለስ ስህተቴን ለመማር እጥራለሁ፡፡ | | | | |
| 32. | በንግግር ወይም በጽህፈት ልምምድ ወቅት ለሰዋስዋዊ ህግጋት ልዩ ትኩረት በመስጠት | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እማራለሁ፡ | | | | |
| 33. | የሰዋስው ስህተቶቼን በማስታወስ የስህተት ምንጭ የሆኑትን ምክንያቶች በተደራጀ ሁኔታ ለመለየት ሙከራ አደርጋለሁ። | | | | |
| | ክፍል አምስት፦ ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች | | | | |
| 34. | አማርኛ ቋንቋን ለመናገር የሚያስፈሩኝ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን እንደምሰራ ባውቅም ራሴን አደፋፍራለሁ። | | | | |
| 35. | ከከምባትኛ ቋንቋ አቻ የሆኑ የአማርኛ ሰዋሰው መዋቅሮች ሳገኝ ደስ እያለኝ እማራቸዋለሁ። | | | | |
| 36. | አዳዲስ የሰዋሰው ይዘቶችን ስማር ትምህርቱን ከተረደሁት ራሴን አደንቃለሁ። | | | | |
| 37. | አዳዲስ የሰዋሰው መዋቅሮችን በጨዋታና በእንቅስቃሴ ስማር ጭንቀት አይሰማኝም። | | | | |
| | ክፍል ስድስት፦ ማህበራዊ ብልሃቶች | | | | |
| 38. | መምህሬ ስለ አዲሱ የቋንቋ መዋቅር የሚያደርጉት ገለፃ ካልገባኝ ከክፍል ጓደኞቼ ድጋፍ በመጠየቅ እረዳለሁ። | | | | |
| 39. | አዳዲስ የሰዋሰው ትምህርት ባጋጠመኝ ጊዜ ህጎችን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ሰጥቼ ስለመዋቅሩ ለመገንዘብ ጥረት አደርጋለሁ። | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 40. | መምህሬ እኔ የምሰራቸውን ሰዋሰዋዊ ስህተቶች እዲያስተካክሉልኝ እጠይቃለሁ፡፡ | | | | |
| 41. | የሰዋስው መዋቅሮችን ከጓደኛዬ ጋር በመሆን አጠናለሁ፡፡ | | | | |
| 42. | አማርኛ ቋንቋን ለንግግር ስጠቀም የሚገጥሙኝን የሰዋስው ስህተቶች ከእኔ የተሸሉ ተማሪዎች እንዲያስተካክሉልኝ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |

አባሪ 2

**ለተማሪዎች የቀረበቃለ መጠይቅ**

*<u>መመሪያ ሶስት፦ ሰዋስውን ለመ</u>ማር ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው ሰዋስው የመማር ብልሃቶች የቃል መጠይቅ።*

1. በቅርቡ የተማራችሁትን ትምህርት ስራት አስቡ፣ ሰዋሰውን ለመረዳት ለማስታወስ ይረዳችሁ ዘንድ የተጠቀማችኋቸው ዘዴዎች አሉ? ለምሳሌ፣ በርዕስ ግንኙነት፣ በፍቺ ተመሳሳይነት ወይም ተቃራኒ ማደራጀት ሊሆን ይችላል፣ ካሉ እንዴት አደራጃችሁ? ለምን?
2. ቀደም ብላችሁ የተማራችሁትን ሰዋስው በቀላሉ ለማስታወስ ክለሳ ታደርጋላችሁ? እንዴትስ ነው የምትከልሱት?
3. የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በቀላሉ ለመረዳት ለማስታወስ በከምባትኛ ወይም በሌላ ቋንቋ ውስጥ ከምታውቁት ሰዋስው ጋር አያይዛችሁ ለመማርና ለማስተወስ ሞክራችሁ ታውቃላችሁ?
4. የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ዕውቀታችሁን ለማዳበር ጥረት ታደርጋላችሁ? መልሳችሁ "አዎን" ከሆነ ምን አይነት ተግባራትን አከናዎናችሁ?
5. የሰዋስው ዕውቀታችሁን ለማዳበር በሚል አላማ ከመማርያ ክፍል ውጪ የአማርኛ ጽሁፎችን (ለምሳሌ፡- ልበ ወለዶች፣ግጥሞች፣ መጽሄቶችን ወዘተ ታነባላችሁ? የምታነቡት አልፎ አልፎ ነው ወይስ ሁል ጊዜ ነው? ባይበልጥ የምታተኩሩበት በየትኛው ለይ ነው? ለምን?
6. የሰዋስው ዕውቀታችሁን ለማዳበር ይረዳችሁ ዘንድ የአማርኛ ሬድዮ፣ የቴሌቪዢንን ግግሮችን፣በቴፕ የተቀረጹ ንግግሮችን ታዳምጣላችሁ? የምታዳምጡት በየቀኑ ወይስ አልፎ አልፎ ነው?
7. የአማርኛ ጽሁፎችን ስታነቡ ወይም ንግግሮችን ስታዳምጡ፣ ምንነታቸውን የማታውቋቸው አዳዲስ የሰዋስው ትምህርቶች (ለምሳሌ አረፍተ ነገሮችን መስራት፣ ሀረጋትን መስራት ትክክለኛውን የቃላትና ሀረጋትን አገባብ ማወቅና ወዘተ) ስታገኙ ምንታ ደርጋላችሁ? አዲሱን ሰዋስው ይዛችሁ አገባባቸውን የተለያዩ ማጣቀሻዎችን በመጠቀም ትረዳላችሁ? ወይስ ከአገባባቸው ለመገመት ትሞክራላችሁ? ወይስ ሌሎች ሰዎችን ለምሳሌ መምህራን ወይም ጓደኞቻችሁን ትጠይቃላችሁ? ወይስ ትተዋቸዋላችሁ?

8. የአማርኛ ጽሁፎችን ስታነቡ ወይም ንግግሮችን ስታዳምጡ፣ በአጠቃላይ ከማንኛውም ምንጭ የምታገኟቸውን አዳዲስየ አማርኛ ሰዋስው በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግባችውት ይዛላችሁ? እንዴት ስነው የምትመዘግቡት?
9. የሰዋስው ዕውቀታችሁን ለማዳበር አዳዲስ ሰዋስውን የምታጠኑበት ዕለታዊ ወይም ሳምንታዊ ወይም ሌላ ፕሮግራም አላችሁ?
10. የአማርኛ የሰዋስው ዕውቀታችሁን ለማዳበር ከላይ ከተዘረዘሩት አጋዥ ሰዋስውን የመማር ብልሃቶች በተጨማሪ የተጠቀማችውባቸው ብልሃቶች አሉን? ካሉ የትኞቹ ናቸው?